# አዲስ ዘመን

እንድ

ረቡዕ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 348 ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ዳኒ አበራ

## "ኢትዮጵያ በልጆቿ ብርታት እያሸነፈች ወደ አዲስ ከፍታ ትሻገራለች"

\- ዶክተር ለገሰ ቱሉ
የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

በኃይሉ አበራ

አዲስ አባበ፡- ኢትዮጵያ በብዙ ፈተና ውስጥ ሆናም በልጆቿ ብርታት እያሸነፈች ወደ አዲስ ከፍታ እየተሸጋገረች ነው ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "የሚድያ ሚና ስለኢትዮጵያ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ በጎንደር ከተማ ባዘጋጀው ዘጠነኛው "ስለኢትዮጵያ" የፓናል ውይይት ላይ ዶክተር ለገሰ እንደተናገሩት ኢትዮጵያ በልጆቿ ብርታት እያሸነፈች ወደ አዲስ ከፍታ እየተሸጋገረች ባለችበት በዚህ ወቅት የሚዲያው አስተዋጽኦ የጎላ ነው፡፡

ብሔራዊ ጥቅምን በማረጋገጥ፣ ሕብረ ብሔራዊ አንድነትን እና ወንድማማችነትን በመገንባት ብሔራዊ መግባባትን በመፍጠር ረገድ ሚዲያዎች እና የሚዲያ ተዋንያን ሚና ከፍተኛ መሆኑንም አመላክተዋል።

ዶክተር ለገሰ እንደተናገሩት፤ የዛሬ አንድ ዓመት በሀገር ውስጥ ሁሉም "የሜይን ስትሪም" እና የማሕበራዊ ሚዲያዎች ኢትዮጵያ የገጠማትን ችግር አንድ ሆነው

"ኢትዮጵያ በልጆቿ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሕብረተሰቡ የዓባይ ግድብን ለማጠናቀቅ ርብርብ እንዲያደርግ ጥሪ ቀረበ

\- ግድቡን ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ሕብረተሰቡ የዓባይ ግድብ ግንባታና ውሃ ሙሌት የደረሰበትን ደረጃ በመመልከት በበለጠ ወኔና በላቀ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለግድቡ ፍፃሜ እንዲረባረብ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ጥሪ አቀረበ፡፡ ግድቡን ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግም ተነግሯል፡፡

ለዓባይ ግድብ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል ያለመ የሕዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ የማስጀመሪያ መርሀ ግብርን በተመለከተ በትናንትናው ዕለት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዛግዌ ቅርንጫፍ አዳራሽ በተሰጠው መግለጫ ላይ የጽህፈት ቤቱ የሚዲያና ኮምኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም እንደገለጹት፤ ግድቡ ከተጀመረ ጀምሮ በተለያዩ መንገዶች ከ17 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

እንደ አቶ ኃይሉ ገለፃ፤ በሀገር ውስጥ ቦንድ ግዢና ልገሳ 15 ቢሊዮን ብር፤ የዲያስፖራ ቦንድና ልገሳ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በልዩ ልዩ ገቢዎች ከ571 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል፡፡ በ8100 የፅሁፍ

ሕብረተሰቡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ












## ለአገራዊ ምክክሩ መሳካት መወያየት መለመድና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተገለጸ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ የነገዋን ኢትዮጵያ የሚወስን አጀንዳ በመሆኑ ለምክክሩ መሳካት መወያየትና በጋራ ለመስራት መንቀሳቀስ መለመድና ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉ የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤት የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማሕበራት ዘርፍ ኃላፊ ዶክተር ዓለሙ ስሜ አስታወቁ፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ላይ ውይይት ባካሄዱበት ወቅት የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤት የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማሕበራት ዘርፍ ኃላፊ ዶክተር ዓለሙ ስሜ

ለአገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






### በአዲስ አበባ በ 7 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ ነው

ገጽ 4

# ሠራዊቱን በተመለከተ ያልተገቡ መረጃዎችን የሚያራግቡ አካላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማሳሰቢያ ተሰጠ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የሠራዊቱን ወቅታዊ ሁኔታ ባልተረጋገጡ፣ ባልተገቡ መረጃዎችና አሉባልታዎች የመዘገብ ወይም የማራገብ አሉታዊ ሙከራዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙና ያልተገቡ መረጃዎችን የሚያራግቡ አካላትም ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር አሳሰበ።

ሚኒስቴሩ ትናንትና ባወጣው መግለጫ እንዳሳሰበው፤ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተዛባ፣ ተገቢ ያልሆነና መከላከያን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ዘገባ የሚሰሩ የማሕበራዊ ሚዲያ አካላት ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል።

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ ከሰሞኑ ግልፅ አደጋ ለመፍጠር በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ሰርጎ የገባው አልሸባብ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኃይሉ መደምሰሱ ይታወቃል። በሰሜኑ የሀገሪቷ ክፍልም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ይገኛል። በተለይ የአሸባሪው ሕወሓት አፈ ቀላጤዎች በሰሞነኛ ሰበካቸው የሰራዊታችን ስም ማጥፋት ስራዬ ብለው ተያይዘውተዋል።

ተቀባይነት የሌላቸውን ሰበቦች በመደርደር መከላከያ ሠራዊታችንን በመወንጀል ዘመቻ መሰማራታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው ያለው መግለጫው፤ ለዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጭምር "የሰላም ድርድሩ ቴክኒካል ፈርሷል፣ መከላከያ ኃይሉን እያስጠጋና በከባድ መሳሪያ እየደበደበን ነው የሚሉ አሉባልታዎችና የቅድመ ግጭት ፕሮፖጋንዳዎች እያስተጋቡ መሆኑን ጠቁሟል።

የጠላትን ሴራ እና አጀንዳ በውል ተገንዝበው የሚሞግቱ ሚዲያዎች የመኖራቸውን ያህል አንዳንድ የማሕበራዊ ሚዲያ ዘገባዎችና መረጃዎች ይህንኑ አፍራሽ ውንጀላ ባልተገባም መልኩ እየተቀባበሉት መሆኑን ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

ያለበቂ መረጃ የጠላትን እንቅስቃሴ መዘገብ በራሱ የሕዝባችንን የዕለት ከዕለት ኑሮ ያውካል ያለው መከላከያ፤ ጠላት በዚህ ገባ፣ በዚህ ወጣ ፤ የወገን ሠራዊት በዚህ ገባ፣ በዚህ ወጣ የሚለው ወሬ በፍፁም ዜናና የዜና ትንታኔ ሊሆን አይችልም ሲልም በመግለጫው አሳስቧል።

ጦርነቱን እንዲዘግቡ ፍቃድ ከተሰጣቸው ውጪ በሀገር ህልውና ላይ የተቃጣን ጦርነት የሚያክል ነገር በማህበራዊ ሚዲያ ገቢ ማስገኛነት በሚል ያልተረጋገጠ መረጃ ይዞ ወሬውን ማናፈስ የሕዝባችንን መረጋጋት የሚነሳ ጉዳይ ነው ፤ የፀጥታ ሃይሎችን ተግባርንም ያውካልና አግባብ አይደለም ሲል በመግለጫው አስፍሯል።

የሠራዊታችን ወቅታዊ ሁኔታና እንቅስቃሴ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ለሕዝባችን ይፋ ስናደርግ እንደነበረው ወደፊትም በዚሁ አግባብ የሚከናወን ይኖራል ያለው መከላከያ፤ ሠራዊታችን ማንኛውንም ጥቃት ለመመከት በፅናትና በጥንቃቄ፤ ተዘጋጅቶ በተጠንቀቅ በቆመበት በአሁኑ ወቅት ጠላት ባሰናዳው ፕሮፖጋንዳ ወጥመድ የተጠለፉ አሉታዊ መረጃዎች ማስተጋባት እንደማያስፈልግ መልዕክት አስተላልፏል።

ይሁንና በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች የሠራዊታችንን እንቅስቃሴ በማሰራጨት ኃላፊነት የጎደላቸው አካላት እንዳሉም አይተናል ፤ ይህ ድርጊት በሠራዊታችን የግዳጅ አፈፃፀም ላይ ምንም አወንታዊ ተፅኖ ሊኖረው ባይችልም ይህንን ተግባር በግዴለሽነት ወይም በማንአለብኝነት የሚቀጥሉና የማይታረሙ ካሉ መከላከያ ሕጋዊ ርምጃ ይወስዳል ሲል አሳስቧል።

የሠራዊቱን ምስጢር በመንዛት፣ የጠላትን አጀንዳ በማራገብ የሀገር ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥሉትን እንደ አስፈላጊነቱ የወንጀል ክስ በመመስረት ተጠያቂ እንደሚደረጉም አስታውቋል።

ወደፊትም ጠላቶቻችን የሚደግሱልንን ሴራ እና ወጥመድ አውቀን በማክሸፍ ለዕኩይ ዓላማቸው የማንበገር መሆናችንን በተግባር እያሳየን እንቀጥላለን ሲል ገልጿል።

በመግለጫው እንደተመላከተው፤ መከላከያ ሠራዊት የሀገር ሉዓላዊነትን ለመጠበቅ የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት እንዲወጣ የሕዝቡ ድጋፍና ተሳትፎ ጠንካራ መሆኑን ያምናል። በእስካሁኑም ጥረት በሕዝቡና በሠራዊቱ መካከል የተገነባው መተማመንና መደጋገፍ በፅኑ መሰረት ላይ የቆመ በመሆኑም ፈተናዎች በጋራ በማለፍ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት የማስከበር ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል።

# ምርጫ ቦርድ ኢሠፓ በፓርቲነት እንዳይመዘገብ አገደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ) በሚል ስያሜ የሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ እንደማይሰጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሠረት "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ)" በሚል ስያሜ የሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱ አካላት መኖራቸውን ገልጿል።

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ መሰረት የምዝገባ ጥያቄ የቀረበበት የፓርቲ ስያሜ ቀድሞ ህጋዊ ሰውነት ከነበረው ፓርቲ ስያሜ ጋር በመመሳሰል በመራጮች ዘንድ ግርታን የሚፈጥር ሆኖ ከተገኘ ቦርዱ የምዝገባ ጥያቄውን ሊቀበል እንዳልቻለ አስታውቋል።

በሌላ በኩል በኢ.ህ.ድ.ሪ ሕገመንግሥት በአገሪቱ በብቸኛነት እንዲንቀሳቀስ ዕውቅና ተሰጥቶት ገዢ ፓርቲ የነበረ የፖለቲካ ድርጅት በዚሁ ስያሜ ይጠራ እንደነበረ ቦርዱ አስታውሶ፤ በግንቦት 1983 ዓ.ም የዚህን ፓርቲ ከሥልጣን መውረድ ተከትሎ ስለ ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ሥነ ሥርዓት የወጣው አዋጅ ቁጥር 3/83 (አልተሻረም) አንቀጽ 8(2) ኢሠፓ የተባለው ድርጅት ፀረ-ዴሞክራሲ እና ወንጀለኛ ድርጅት ነው፤ በሚል በሕግ መፍረሱን ጠቁሟል።

በመሆኑም አሁን ለቦርዱ የምዝገባ ጥያቄ የቀረበበት የፓርቲ ስያሜ የሚመሳሰለው በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መስክ ህልው ከነበረ ድርጅት ጋር ብቻ ሳይሆን አሁንም ፀንቶ ባለ ሕግ ወንጀለኛ ተብሎ ብያኔ ካረፈበት ብሎም ከፈረሰ ድርጅት ጋር መሆኑን ቦርዱ አጽንኦት ሰጥቷል።

በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የምዝገባ ጥያቄውን ቦርዱ ቢቀበል ያለተሻረ ሕግ እንደተሻረ እንዲሁም በሕግ የፈረሰ ድርጅት የሕግ ገደቡ ታልፎ እገደገና እንደተቋቋመ የሚያስመስል የሕዝብ እይታ ሊፈጥር እንደሚችል ቦርዱ አስረድቷል።

ባለፉት ሳምንታት ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በመደበኛም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ የተነሱት ሃሳቦችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል።

ይህን አይነት የሕዝብ እይታ በምርጫ ወቅት መራጮችን ወደሚያምታታ መረጃ እና አረዳድ ማደጉ ስለማይቀር ቦርዱ "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ (ኢሠፓ)'" በሚል ስያሜ ሀገራዊ ፓርቲ ለማስመዝገብ የቀረበለትን ጥያቄ በምርጫ አዋጁ አገቀፅ 69(ለ) መሰረት ውድቅ በማድረግ ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ መወሰኑን አስታውቋል።

ይሁንና የፓርቲውን ምዝገባ ጥያቄውን ያቀረቡት አስተባባሪዎች በሌላ ስያሜ ዓላማቸውን ለማራመድ ፓርቲ የማደራጀት እና በሕጉ መሰረት ሲመዘገብም የፖለቲካ እንቅስቃሴ የማድረግ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ቦርዱ ገልጿል፡፡

# በዓላትን በአግባቡ በመንከባከብ ማንነትን በሚገልጽ መልኩ ማሳደግ እንደሚገባ ርዕሰ መስተዳድሩ አሳሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


ዶክተር ይልቃል ከፋለ

አዲስ አበባ፡- ሃይማታዊም ሆነ ባህላዊ በዓላትን በአግባቡ በመንከባከብ ማንነትን በሚገልጽ መልኩ ማሳደግ እንደሚገባ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ አሳሰቡ። የአሸንድዬ በዓል በላልይበላ ከተማ ተከብሯል።

በበዓሉ ላይ መልእክት ያስተላለፉት ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ድንቅና ብርቅ የሆኑ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት የሚከበሩባት ሀገር ናት። በመሆኑም እነዚህን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት በአግባቡ በመንከባከብ ማንነትን በሚገልጽ መልኩ ማሳደግ ይገባል።

የኢትዮጵያን ጸጋዎች በአግባቡ ባለመጠቀማችን አሁንም በድህነት እንኖራለን ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ ድህነት ክፉ በሽታ በመሆኑ ለማሸነፍ የሁሉንም ትግልና ጥረት ይጠይቃል ብለዋል።

መንግሥት ድህነትን ለማስወገድ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችን ነድፎ እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል። አንደኛው ድህነትን የመታገያ መንገድም ቱሪዝምን ማስፋፋት እንደሆነ ነው ያነሱት።

ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝና የአሸባሪው ሕወሓት ወረራ በዓላት እንዳይከበሩ እንቅፋት ፈጥሮ መቆየቱን ገልጸው፤ ሕዝቡ ታላቅ ሥነ ልቦና ያለው፣ አሸናፊነትን የተላበሰ በመሆኑ የደረሰበትን ውድመት በትግልና በጥረት እተካዋለሁ የሚል ሥነልቦና ያለው ታላቅ ሕዝብ ነውም ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን በትጋት ከሠሩ ድህነትን እንሻገረዋለን ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ልማትን ለማፋጠን እና ድህነትን ለመቅረፍ ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ነው የተናገሩት።

ያለ ሰላም ልማት አይኖርም፤ በዓላትን ማክበርና ውብ የሆነውን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥርዓትን ለዓለም ማሳየትም አይቻልም ሲሉ ተናግረዋል።

እያንዳንዱ ዜጋ ሰላምን የማስጠበቅ ሃላፊነት እንዳለበት ያስገነዘቡት ዶክተር ይልቃል፤ ሰላምን በማረጋገጥ ድህነትን ለመቅረፍ በትጋት መሥራት ይገባልም ብለዋል።

ላስታና አካባቢው በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ምክንያት በመብራት እጦት እየተሰቃየ ያለ መሆኑንም አንስተው የሚያዋጣን በአንድነት መቆም ነው ብለዋል።

በአንድነት በመቆማችን ወረራውን ቀልብሰን ሕልውናችንን እንድናረጋግጥ አስችሎናል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በአንድነት ከቆምን የሚደፍረን ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ሃይል የለም፤ ከመጣም እንደተለመደው አከርካሪውን ሰብረን መመለስ እንችላለን ነው ያሉት። ለአንድነት ትልቅ ዋጋና ክብር በመስጠት መሥራት ይገባልም ብለዋል።

"መለያየት የግጭት መንገድ ነው፣ ግጭት የድህነት መንገድ ነው፣ ግጭት ባሕላችንና ሃይማኖታችንን በድምቀት እንዳናከብር የሚያደርግ በጥላቻ የተመሠረተ አክሳሪ ተግባር ነው"ም ብለዋል። ከግጭት የሚገኝ ትርፍ አለመኖሩንም አንስተዋል።

ከግጭት ሞት፣ ስደትና ንብረት ውድመት ብቻ እንደሚገኝም ገልጸው፤ ግጭትን መጸየፍ አለብን ብለዋል። ተከባብረን እና ተደማምጠን ከሠራን የማንሻገረው ፈተና የለም፤ የአሸንድዬ በዓል ማደግና መስፋት ይገባዋል ሲሉም ገልጸዋል።

በዓሉን በዓለም ማስተዋወቅ ይገባል ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ ዓለም በዓሉን እንዲያውቅ እናደርገዋለንም ነው ያሉት። በዓሉን ሀብት እንፈጥርበታለን፣ ልማት እናፋጥንበታለንም ብለዋል። ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በመፍታት ከችግር መውጣት እንደሚገባም ገልጸዋል። በዓሉ ሕዝቡ በተስፋ እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑንም አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ባሕልና እሴትን በመጠበቅ በኩል እያደረገችው ላለው ተግባር ምሥጋና ይገባታል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በዓሉን ሌሎች እንዲመጡና እንዲጎበኙት ማድረግ ይገባልም ነው ያሉት። በዓሉ የኢትዮጵያን መጪ ዘመን ብሩህ እንደሆነ ተስፋ የሚሰጥ መሆኑንም መናገራቸውን አሚኮ ዘግቧል።

# ላልይበላን የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ላልይበላ የዓለም ቅርስነቱን ባስጠበቀ መልኩ የቱሪዝም ልማት ማዕከል ለማድረግ የፌዴራል መንግሥቱ እየሰራ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ተናገሩ።

የአሸንድዬ በዓል በላልይበላ ከተማ "አሸንድዬ የማንነታችን እና የአንድነታችን መስተጋብር ነው" በሚል መሪ መልዕክት ትናንትና ሲከበር አቶ ደመቀ እንደተናገሩት፤ የላልይበላን ቅርስ የዓለም ቱሪስት መዳረሻነት ባገናዘበ መልኩ ደረጃውን የጠበቀ ሥራ እንዲከናወን የፌዴራል መንግሥት ጥረት ያደርጋል።

ላልይበላ አሁንም ድረስ ዓለም የሚደመምበት እና ኢትዮጵያ ይበልጥ የምትታወቅበት ውብ የኪነ ጥበብ ማእከል ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፤ ታሪክን ማንሳት እና ማውሳት ብቻውን በቂ አይደለም ብለዋል፡፡ በመሆኑም ዓለም የሚደመምበትን የቅዱስ ላልይበላ ኪነ-ሕንፃ ጠብቆና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ የአሁኑ ትውልድ ትልቅ ሃላፊነት አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ይህንን ድንቅ የታሪክ፣ የባሕል፣ የሃይማኖት እና የቀደምትነት ማእከል ይበልጥ አልምቶ ሕዝብንም ሀገርንም ተጠቃሚ ማድረግ በዚህ ትውልድ ትከሻ ላይ ያረፈ ሃላፊነት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አበርክቶዋ ብዙ ነው ያሉት አቶ ደመቀ በትብብር እና በመቀራረብ ጸጋዎችን አልምቶ የገቢ ምንጭ ማድረግ ደግሞ መንግሥት በዘርፉ ላይ ያስቀመጣቸው የሥራ ሃላፊዎች ተቀዳሚ ተልዕኮ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ደመቀ እንዳስትወቁት፤ የላልይበላን ኪነ ሕንፃ አደጋ ተጋላጭነት እንዳይስፋፋና ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍም የፌዴራሉ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የክልሉ መንግሥትና ሕብረተሰቡ በቅንጅት ይሰራሉ። ከአባቶቻችን የተወረሰው ድንቅ ባህልና ኪነ ጥበብ የአሁኑ ትውልድም የበለጠ እንዲሰራበት ጥረት ይደረጋል።

የቅዱሳንና የንጉሣን መናገሻ የሆነችውን ላልይበላ ከተሰጡን ጸጋዎች መካከል አንዷ ናት ያሉት አቶ ደመቀ፤ ላልይበላን የቱሪዝም ማዕከል እና የዓለም ሕዝብ መዳረሻ ለማድረግ እንሰራለን ብለዋል፡፡

የላልይበላ ከተማ ነዋሪም ለቱሪዝም ዘርፉ የሚመጥን ተግባር ሊያጠናክር እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሰው ሠራሽ እና በተፈጥሯዊ ችግሮች ምክንያት አካባቢው መጎዳቱን የገለጹት አቶ ደመቀ ከጦርነቱ ማግስት ልደትን በላልይበላ ማክበራችን ኢትዮጵያውያን ያለንን የሥነ ልቦና ጥንካሬ ያመላከተ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ልደትን ትናንት እና አሸንድዬን ዛሬ በአደባባይ ወጥተን እንድናከብር የሕይወት እና የአካል መስዋእትነት ለከፈሉ ጀግኖች፤ ለሃይማኖት አባቶች ክብር እና ፍቅር አለን ብለዋል።

በጦርነት ተወልደው በጦርነት ጥቅማቸውን ለማስከበር ትናንት ኢትዮጵያ ላይ ክህደት የፈጸሙ ሃይሎች ዛሬም ዳግም ጦርነት በመጎሰም ላይ ናቸው ያሉት አቶ ደመቀ ኢትዮጵያ የሰላም አማራጮችን እስከ መጨረሻው እንደምትጠቀም ጠቁመዋል።

"ኢትዮጵያ ጦርነት ይበቃታል፤ ኢትዮጵያውያንም ጦርነት ይበቃቸዋል" ያሉት አቶ ደመቀ የሕዝብን ሕይወት የሚለውጡ እና የሀገርን ብልጽግና የሚያረጋግጡ ብዙ ተስፋዎች ስላሉን ተረጋግተን የምንሠራበት እድል እንፈልጋለን። ነገር ግን ተገቢ ላልሆነ የበላይነት እና ለኢ-ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የምንደራደርበት ትዕግስት የለም ብለዋል፡፡


ወጣት ሉምቤቦ ሰለሞን


ወጣት አባንግ ኩመዳን


ወጣት አብርሃም ታደሰ

# ውይይቱ በሀገራዊ ልማት ውስጥ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ መነሳሳት እንደፈጠረባቸው ወጣቶች ተናገሩ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር በወጣቶች ሚና ዙሪያ ያደረጉት ውይይት በሀገራዊ ልማት ውስጥ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ከፍተኛ መነሳሳት የፈጠረባቸው መሆኑን በውይይቱ ላይ የተሳተፉ ወጣቶች ተናገሩ፡፡ከውይይቱ በፊት የተመለከቷቸው የልማት ስራዎች ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥም ሆና በከፍተኛ ደረጃ እያደገች መሆኗን የተረዱበት እንደነበረም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ተማሪዎች ህብረት ዋና ጸሐፊ ወጣት ሎምቤቦ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ ወጣቱ በውይይቱ የጥፋት ሃይሎች ጉዳይ አስፈጻሚ እንዳልሆነና ሀገርን ለማሳደግ ወጣቱ የራሱን አሻራ ማሳረፍ እንዳለበት መረዳት መቻሉን ገልጿል።

ኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ እያደገች ያለች ሀገር መሆኗን እንደተረዳ የገለጸው ወጣት ሎምቤቦ፣ የጎበኙዋቸው ፕሮጀክቶች የዚህ ማሳያ ናቸው ብሏል። ወጣቱ ደግሞ እኛ ያየናቸውን እያየ ሲመጣ በሚዲያዎች የሚወራውና መሬት ላይ ያለው ሀቅ የተለያየ እንደሆነ እንደሚረዳና ለስራዎች ከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚያሳይ አልጠራጠርም ሲልም ተናግሯል።

ከዚህ በፊት ወጣቱ በልማት ስራዎችና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የራሱን አሻራ እንዳያስቀምጥ ይደረግ ነበር ያለው ወጣት ሎምቤቦ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በውይይቱ አማካኝነት ይህንን ሊያስቆም የሚችል ሥርዓትን መዘርጋት ችለዋል ብሏል።

ኢትዮጵያ መልማትና ማደግ የምትችል ሀገር እንደሆነችና ያላትን ወጣት ተጠቅማ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር የምትችል ሀገር እንደምትሆን ከውይይቱ መረዳት ችያለሁ ያለው ወጣት ሎምቤቦ፣ ውይይቱ እንደሀገር ወጣቱ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ሆኖ የራሱን አሻራ እንዲያስቀምጥና እንዲነሳሳ የሚያደርግ እንደሆነ ጠቅሷል።

እኛ ወጣቶች በሀገር ደረጃ እንደዚህ ተወያይተን ለሀገራዊ ስራዎች እንድንሳተፍ ይህንን የውይይት መድረክ ላዘጋጁልን አካላት ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል።

ከጋምቤላ ክልል ውይይቱን ለመሳተፍ የመጣችው ወጣት አባንግ ኩመዳን በበኩሏ፣ በውይይቱ ኢትዮጵያ በየጊዜው የተለያዩ ችግሮች ውስጥ ብትሆንም ወጣቱ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ እርስ በእርስ በመደጋገፍና በመረዳዳት የነገ የሀገር ተረካቢ ትውልድ መሆኑን አለመዘንጋቱን መረዳት ችያለሁ ብላለች። ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የተውጣጡ ወጣቶች በውይይቱ ተሳተፊ በመሆናቸው ውይይቱ ህብረብሔራዊ አንድነቱን እንዲጠብቅ አድርጎታል ስትልም አክላለች።

የኛ ዘመን ወጣት እንዲህ ማድረግ ነበረብኝ፤ እንዲህ ሳላደርግ ጊዜ አለፈብኝ ከማለቱ በፊት አሁን ላይ ማድረግ የሚገባውን አድርጎና እራሱ ቆጥቦ መኖር አለበት ያለችው ወጣት አባንግ፣ ወጣቱ በሚገባው ልክ መስራት እንዳለበትና ሀገር አፍራሽ ከሆኑ ድርጊቶች መታቀብ እንደሚኖርበት አስገንዝባለች፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩም በውይይቱ ሀገር ጠባቂና ገንቢ ንግግር መናገራቸው ወጣቱ ከዛሬ ጀምሮ ለሀገር እድገት ጠንክሮና ተግቶ እንዲሰራ ያደርገዋል፤ ይህም ውይይቱ ላይ የተሳተፉ ወጣቶች ሀገርን ከማፍረስ ይልቅ ለመገንባት አቅጣጫን የሚያሳይ ነው ስትል የውይይቱን ፍሬያማነት ተናግራለች።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንትና የውይይቱ ተሳታፊ ወጣት አብርሃም ታደሰ በበኩሉ፣ ውይይቱ ብዙ ጥቅሞችን የሚያስገኝና ወደፊት ሀገርን ሊያሻግር የሚችል ተስፋ የሚሰንቅ ነበር ብሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካላቸው ትንሽ ጊዜ ውስጥ ጆሯቸውን ለኛ ስጥተው የኛን ጥያቄዎች አዳምጠው የተነሱላቸውን ጥያቄዎች በሚገባ መልስ ሰጥተዋል ያለው ወጣት አብርሃም፣ ውይይቱ በወጣትነቴ ለሀገሬ ሚጠበቅብኝን ማድረግ እንዳለብኝና ስለሀገሬ ያለኝ አመለካከት እንዲለመልም አድርጎኛል ብሏል።

ወጣት ለልማትም ለጥፋትም ቅርብ ነውና ጥፋቱን ትተን ልማቱ ላይ ትኩረት አድርገን ብንሰራ መልካም ነው። መንግሥት ለልማት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ከሆነ እኛ ወጣቶች ደግሞ የሚጠበቅብንን ማድረግ መቻል አለብን ብሏል።

ወጣቱ ብዙ አቅም ያለው በመሆኑ ሀገር ለማሳደግ የሚችሉ ስራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ ከማይረቡ ጉዳዮችና አሉባልታዎች ራሱን አቅቦ እንዲኖር ያስችለዋል። ይህን ደግሞ ወጣቱ ከወሬ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ያደርገዋል። ስለዚህ ሁሉም ወጣት ዛሬውኑ ወደ ተግባር ቢገባ ሀገራችን አሁን ካለንበት አንድ ደረጃ ከፍ እንላለን ብሏል።

ወጣት አብርሃም እንደተናገረው፤ "አዲስ አበባ ከመምጣቴ በፊት ኢትዮጵያ በጦርነት ላይ ስለነበረች፤ ልማት የለም የሚል ሃሳብ ይዤ ነበር የመጣሁት፤ በጎበኘኋቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች ግን ኢትዮጵያ እያደገችና እየለመለመች ያለች ሀገር መሆኗን መረዳት ችያለሁ" ብሏል።

# የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም ዋጋ በመስጠት የሄደበት ርቀት የሚደነቅ መሆኑ ተገለጸ

ዳግማዊት ግርማ

ደብረታቦር፡- መንግሥት ለሰላም ዋጋ በመስጠት የሄደበትን ርቀት አደንቃለሁ ሲሉ የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻው ተናገሩ። ፕሬዚዳንቱ ሕብረተሰቡ የትኛውንም አይነት ለሀገር ሉአላዊነት ፀር የሆነን አካል ሊታገስ እንደማይገባም ነው የገለጹት።

ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሕወሓት ጋር በተያያዘ ያለው ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን የሚያደርገው ጥረት የሚያስደንቀው ነው።

እንደ ዶክተር አነጋግረኝ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦርነትን ክፉ ገጽታ በመረዳት ሀገር ለዳግም ጦርነት እንዳትሄድ ሰላምን ሽቶ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሕወሓት ቀደም ሲል በሕዝብና ሀገር ላይ ያደረሰውን በደል ሳይቆጥር የሰላም እጆቹን ለቡድኑ መዘርጋቱ ከአስተዋይነት የመነጨ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር አነጋግረኝ፤ የሽብር ቡድኑ ለሰላም የተዘረጋለትን እጅ ማሳጠፍ እንደማይገባውም ገልጸዋል።

ሕወሓት የቀረበለትን የሰላም አማራጭ ያለመቀበል አዝማሚያ እንደሚታይበት የገለጹት ዶክተር አነጋግረኝ፤ ሰላምን በማስቀደም ሀገርን ለዳግም ጦርነት ከማነሳሳት መቆጠብ እንደሚገባውም ነው የተናገሩት።

የኢትዮጵያ መንግሥት እያንዳንዱ ጦርነት የሚያሳጣውን የሰው ልጅ ሕይወት እንዲሁም የሚያወድመውን ንብረት ከመረዳትና የትኛውም ጦርነት ሊደገም አይገባም በማለት ለሰላም መንገድ ቅድሚያ መስጠቱ እንደሚያስመሰግነውም ነው የተናገሩት።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሲቪል ማሕበራትን ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችን በመጠቀም እንዲሁም ገለልተኛ ሆኖ የተመሠረተ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በማቋቋም ለሰላማዊ መግባባት በር የከፈተና ሰላምን ምርጫው ያደረገው አካሄድ ተመስጋኝ እንደሚያደርገውም ነው ዶክተር አነጋግረኝ የተናገሩት።

የሰላም አማራጭ ያለመቀበል ችግሩ ከዘለቀና የመንግሥት የሰላም ጥሪ ተቀባይነት ካጣና የጦርነት ጉሰማው ካልቆመ ወደ ማይቀረው ሰላምን የማስከበር ዘመቻ መግባት እንደሚያሻ ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻው ገልጸዋል።

ዶክተር አነጋግረኝ አክለውም ሕብረተሰቡ የትኛውንም አይነት ለሀገር ሉአላዊነት ጸር የሆነን አካል ሊታገስ እንደማይገባም ነው የገለጹት።


ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻው

# በአዲስ አበባ በ7 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በሰባት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የአነስተኛና የመካከለኛ ኢንዱስትሪ ልማትን ለሚያቀላጥፍ የሚረዳ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ ነው። የከተማ አስተዳደሩ ትናንትና የአነስተኛና የመካከለኛ ኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ለማካሄድ ከተቋራጮች ጋር የስምምነት ፊርማ አካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በፊርማ ሥነሥርዓቱ ወቅት፤ ከተማችንን ለማሳደግ አስተዳደሩ ለኢንዱስትሪ ግንባታ እስከ 93 ሄክታር መሬት ማዘጋጀቱ ምን ያህል ለዘርፉ ትኩረት እንደሰጠው አመላካች ነው ብለዋል፡፡

ለአዲስ አበባችን የመጀመሪያና አዲስ ብስራት የሆነ የአነስተኛና መካከለኛ የኢንዱስትሪ ፓርክ መገንባት ስምምነት ፈጽመናል ያሉት ከንቲባዋ፤ ኢትዮጵያ ወደ ምንመኝላት ብልፅግና እንድትጓዝ ኢንዱስትሪን ማስፋፋት፣ የስራ ባህልን መቀየር ፣ አምራችን ማበራከት፣ ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግርን ማረጋገጥ የግድ ይለናል ብለዋል፡፡



የኢንዱስትሪ ፓርኩ ግንባታ ስምምነት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት የሚያግዝ ፣ተኪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሬን የሚያስቀርና በቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸው የላቁ ፣ የስራ ባህላቸው የጎለበቱ ፣አምራች ዜጎችን የሚያፈራ እንደሚሆን ታሳቢ ያደረገ ነው ሲሊ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ በከተማ አስተዳደሩ በጀትና ዕቅድ እንደሚያከናወን ገልጸው፤ የፓርኩ ግንባታ በሁለት ዓመት እንዲጠናቀቅ የውለታ ጊዜ የተያዘለት መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጻ፤ ፓርኩ ሲጠናቀቅ ከአግሮ ፕሮሰሲንግ ጀምሮ የጨርቃ ጨርቅ አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የኮንስትራክሽን፣ የኬሚካል እና ፕላስቲክ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የመድሃኒትና የመድሃኒት ማምረቻ ግብዓቶች የመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች የሚመረቱበት ነው።

በፕሮጀክቱ ግንባታ 21 የተለያየ ወለል ያላቸው ሼዶች፤ 400 የግብዓት አቅራቢዎችና ምርት መሸጫ ሱቆችም ይኖሩታል፤ በአጠቃላይም የኢንዱስትሪ ፓርኩ ከ18 እስከ 20 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኩ ግንባታ ተቋራጮቹ በበኩላቸው ፕሮጀክቱን በውሉ መሰረት ለመጨረስ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ቃል መግባታቸውን የከንቲባ ጽህፈት ቤት በማሕበራዊ የትስስር ገጹ አስታውቋል፡፡

በሰባት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገነባው የኢንዱስትሪ ፓርክ ለዜጎች የስራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ወጣቶች የኢንዱስትሪ ዕውቀት ሽግግር እንዲያገኙ የሚኖረው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑ በፊርማ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ተመላክቷል።

# ሕብረተሰቡ የአባይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መልዕክት እና በቦንድ ሽያጭ እንዲሁም በልገሳ በሀምሌ ወር ብቻ ከ273 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ ተችሏል።

በተለይ በሐምሌ ወር የተሰበሰበው ገንዘብ ከዚህ ቀደም ከነበረው ተሞክሮ አንፃር ከፍ ያለ እንደሆነ ያነሱት አቶ ኃይሉ፤ የግድቡ ሦስተኛ ዙር ሙሌት በስኬት መጠናቀቅና የሁለተኛው ተርባይን ሥራ መጀመር በሕብረተሰቡ ዘንድ መነቃቃት መፍጠሩን ጠቅሰዋል።

ሕብረተሰቡ ቀሪ የአባይ ግድብ ሥራዎችን በስኬት ለማጠናቀቅ እንዲቻል ሀገራዊ ንቅናቄ መጀመሩን አውቆ በተዘጋጁ የግድቡ ሀብት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የግድቡ ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ የግድቡ አፈፃፀም 87 ነጥብ 3 በመቶ መድረሱን ጠቁመው ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን የሕብረተሰቡ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ቀሪ የግድቡ ሥራዎች በሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ እንደሚጠናቀቁ የተናገሩት ኢንጂነር ክፍሌ፤ ሥራውን ለማጠናቀቅ ሕብረተሰቡ በተዘጋጁ የሞባይል መተግበሪያዎች ድጋፍ እንዲያደርግ እና የቦንድ ግዢዎችን እንዲፈፅም አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በበኩላቸው፣ ባንኩ ከግድቡ ጅማሬ ጀምሮ በብድርና በተለያዩ መስኮች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለአባይ ግድብ ብቸኛ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ተቋም ነው ያሉት አቶ አቤ፤ አሁንም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

ሕዝቡም ቦንድ በመግዛትና በባንኩ በመቆጠብ ለአባይ ግድብ መጠናቀቅ ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# "ኢትዮጵያ በልጆቿ ብርታት እያሸነፈች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመመከት ዛሬ ለሰላሟ እንድትበቃ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በተቃራኒው ደግሞ የውጭ ሚዲያዎች ከተመሰረቱበት እሳቤ በመነሳት ኢትዮጵያ ፈርሳለች፤ ከኢትዮጵያ ውጡ፤ ብለው እየዘመሩ የነበረበት ወቅት ነበረ።

ኢትዮጵያ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ በልጆቿ አንድነት እና ሕብረት ሴራዎቹን አክሽፋ ዛሬ ላይ ያለምንም መስተጓጎል የታላቁ ህዳሴ ግድብን ሁለተኛውን ተርባይን አስጀምራ፣ ሶስተኛውን ሙሌትም አከናውና፣ ለዓለም ምሳሌ በሚሆን መልኩ የአረንጓዴ አሻራንም በድል አሳክታለች ብለዋል።

ለበርካታ ዘመናት ከውስጥና ከውጭ በተናጠል እና በቅንጅት የገጠሟትን ፈተናዎች ሁሉ በየጊዜው በሚፈጠሩ ውድ ልጆቿ አበርክቶ ዛሬ በምትገኝበት ከፍታዋ ደርሳለች ሲሉም ተናግረዋል።

በተለያየ የፖለቲካ ሴራ እና ስግብግብነት ኢትዮጵያን ለመቀራመት ያሰፈሰፉ ኃይሎች ከውስጥና ከውጭ ባደረጉት ቅንጅት ኢትዮጵያን የትርምስ ማዕከል ለማድረግና ለመበተን ሲሰራ ነበር ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ በአሁኑ ወቅት ግን እንደ አሸን ፈልተው የነበሩ ከውስጥና ከውጭ የሽብር ኃይል ጋር የተቀናጁ ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ሥርዓት ይዘው፤ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ሰላም የሰፈነባት ሕዝቡ እፎይታ ያገኘችበት ወቅት ላይ ትገኛለች፤ የሚደርሰባትን ጫና በመቋቋም አዎንታዊና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመጣ እየሰራች ነው ብለዋል።

የሚዲያ እና የኮሙኒኬሽን አውታሮች ባለሙያ እና አመራሮች አንድ ላይ ቆመው ኢትዮጵያን አሻግረዋታል ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ብሔራዊ ጥቅም አንዱ የሀገር ሉዓላዊነት እና ድንበርን የማስከበር ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የማሕበራዊ መድረኮች ንቁ ተሳትፎ አድርገው ብሔራዊ ጥቅማቸውን ማስከበር ይጠበቅባቸዋል ሲሉም አሳስበዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ጥቅም የሚከበረው ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ተሳትፎ ሲያደርግ፣ የጋራ ተጠቃሚነት ሲያረጋግጥ ነው፤ በመሆኑም ሚዲያዎች በዚህ በኩል ያላቸው ሚና የላቀ ነው። ለዚህም ውስጣዊ ሁኔታችንን እና የጋራ ተጠቃሚነታችንን አንድ ማድረግ ይገባል።

ሚዲያውም ዜና ከማምረት፣ መረጃን በትንታኔ እና በጽሁፍ ከመስጠት በላይ ኢትዮጵያውያን በአንድ መድረክ በጋራ እንዲቆሙ፣ ከድህነት እንዲላቀቁ፣ ሕብረብሔራዊ አንድነታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያደርጉ የጋራ እሴቶችን መኮትኮት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

ይህንን ለማድረግም ሚዲያዎች በብሔራዊ ጥቅም፣ በጋራ ተጠቃሚነት፣ በሀገራዊ ደህንነት ጉዳዮች በጋራ መሰለፍ መቻል አለባቸው። የሁሉም ሚዲያ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ከሀገሪቱ ሕግና ሥርዓት፣ ከመገናኛ ፖሊሲ እና ከመረጃ ነጻነት አዋጅ ጋር የተቆራኘ በመሆኑም በጋራ በሚያግባቡን ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራት ይችላሉ ሲሉም አጽኦት ሰጥተዋል።

እንደ ዶክተር ለገሰ ገለጻ፤ የሕዝብ ሚዲያው ዋነኛ ዓላማ በመንግሥት የተመረጠን ፖሊሲ ለሕዝብ ማስተዋወቅ፣ አፈጻጸሙን ማሳወቅ፣ ተግዳሮቶቹንና ጉድለቶቹን ማሳወቅ ነው። የግል ሚዲያም የትኩረት መጠኑ ይለያይ እንጂ ለጋራ ሀገራዊ እሴት፣ አንድነት፣ ብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት መረጋገጥ ይሰራሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ ዜጎች ብቻ ሳይሆን እንደ ተደራጀ የዜጎች የጋራ ጥቅም ስብስብ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ተደጋግፈው መሄድ አለባቸውም ብለዋል።

ዶክተር ለገሰ ቱሉ የሚዲያ ነጻነትን አስመልክተው እንደተናገሩት፣ የሚዲያ ነጻነት በኢትዮጵያ እና በአደጉት አገራት እንደየባህሉ የተለያየ ትርጓሜ አለው። በአገራችን የሚዲያ ነጻነት ትርጓሜ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ከሚሰጠው ጠቀሜታ እና የብልጸግና ልዕልና የትኛው መረጃ ያሻግራል ከሚል አንጻር የሚታይ እንጂ ይሄንን የሚጻረር ነጻነት ተቀባይነት የሌለው ነው ብለዋል።

ለሚዲያዎች የሚሰጠው መረጃም ህብረብሔራዊ አንድነትን የሚያመጣ፣ ሰላምን የሚያሰፍን፣ ማሕበራዊ እሴቶችን የሚያጎለብት እንጂ የሚያራርቅ፤ አንዱን አካባቢ ከሌላ ጋር የሚያጋጭ መረጃ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የማይመጠን መሆኑን ተናግረዋል።

በመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሚሰጠው መረጃም የሚታየው መዘግየት የመረጃ ስርጭት እና የመረጃ ቋት ሥርዓት መዘርጋት ስለሚገባ ለዚህ የሚሆን ፖሊሲ እና አሰራር እየተቀረጸ ነው፤ ነገር ግን በፍጥነት ወደ ስራ መግባት ይገባናል ሲሉም ጠቁመዋል።

ሕብረተሰቡ ጠንካራ ዴሞክራሲ እንዲገነባ፤ መንግሥትም ጠንካራ አገር እንዲገነባ ከተፈለገ ጠንካራ ገለልተኛ ተቋማት እና ሚዲያ የሚያስፈልግ በመሆኑ መንግሥት በትኩረት እየሰራበት መሆኑን ገልጸዋል።

የሳይበር ሚዲያውም የዘመኑ ዋነኛ የመረጃ መለዋወጫ አውድ ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ግንባታ ያለው ጠቀሜታ የጎላ በመሆኑ ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋል።

ፌስቡክ፣ ዩቱብ፣ ትዊተርና የመሳሰሉትን በመዝጋት ለውጥ የማይመጣ በመሆኑ ነጻነትን ከኃላፊነት ጋር መውሰድ እንደሚገባ አመልክተዋል።

ማሕበራዊ ሚዲያውና ሳይበር ቴክኖሎጂውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ወደ እሴቶቻችን በማምጣት ላይ የአካዳሚክ ተቋማት፣ ማሕበራት እና ሜይንስትሪም ሚዲያው ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው ሲሉም ተናግረዋል። በሳይበር ሚዲያው ከመንግሥት ተቋሟት ባልተናነሰ የሚሰሩ ግለሰቦች ሊበረታቱ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም በሳይበር ሚዲያው ኋላቀር የፖለቲካ ሁኔታ በመጠቀም ከጎጥ እና ከመንደር በመነሳት ሲሰራበት የቆየውን የኋላቀር የፖለቲካ አስተሳሰብ በሕብረተሰብ ላይ በመጫን የሚሰሩ ኃይሎች አባቶችን፣ ሽማግሌዎችን፣ መሪዎችን በመሳደብ የሚጠቀሙ አሉ ብለዋል።

የሀገር ሉዓላዊነት ሲደፈር፣ በህዳሴ ግድብ ጉዳይ በመሳሰሉት አንድ የሚሆኑት ሚዲያዎቻችን ብሔራዊ ጥቅም ላይም አንድነታቸውን ማስቀጠል እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

# ለአገራዊ ምክክሩ መሳካት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደገለጹት፤ ምክር ቤቶች የሊህቃን ስብስብ ያላቸው በመሆኑ በአገራዊ ምክክሩ ትልቅ ሚና አላቸው። አገራዊ ምክክሩ ደግሞ ሊህቃንን አጥብቆ ይፈልጋል ብለዋል።

አገራዊ ምክክሩ የተሳካ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን ማበርከት አለበት ያሉት ዶክተር ዓለሙ፣ አገራዊ ምክክሩ የነገዋን ኢትዮጵያ የሚወስን አገራዊ አጀንዳ በመሆኑ ለአገራዊ ምክክሩ ስኬት መወያየትና በጋራ ለመስራት መንቀሳቀስ መለመድና ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉም ተናግረዋል።


እንዲሁም ምክር ቤቶች ለአገራዊ ምክክሩ መሳካት ትልቅ ትኩረት መስጠታቸው ጉዳዩን የሚያግዝ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ዛሬ ከያዝነው የፖለቲካ ሽኩቻ በላይ ለመጪው ትውልድ የተሻለች አገር የሚያስተላልፍ በመሆኑ ምክር ቤቶች የሰጡት ትኩረት ተገቢ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዓለሙ ገለጻ፤ መንግሥት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ያስፈልጋታል የሚል ትልቅ እምነት ነበረው። ይህን አቋሙ እውን እንዲሆን የምክክር ኮሚሽን የሚቋቋምበት አዋጅ እንዲወጣ በማድረግ ጥረቶች እንዲቀጥሉ አድርጓል። አገራዊ ምክክሩ ከአዋጁ ጀምሮ አካታችና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያከብር ነው። በምክክሩ ማንም የሚገለልበት ሳይሆን ሃሳብ ያለው እንደ ኢትዮጵያዊ የሚያሳትፍበት ሂደት ነው ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ አገራዊ ምክክሩ ከፖለቲካ አጀንዳ በላይ በመሆኑ ፓርቲዎች ምክክሩ እንዲሳካ የማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው። የሚመለከታቸው አካላት የሚወስኑት ቢሆንም አይስተናገድም የሚባል አጀንዳ አይኖርም፤ ሂደቱን ጠብቆ ተቀባይነት የሚያገኘው ያገኛል፤ የማያገኘውም ይቀራል። ብልጽግናን ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች መገንዘብ ያለባቸው ለትውልድ የሚሆን አገር የማስረከብ ጉዳይ እንጂ የአምስት ዓመት ሥልጣን የመያዝ ጉዳይ ባለመሆኑ ለምክክሩ መሳካት ሁሉም አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር ሄኖክ መለስ በበኩላቸው፤ ሁሉን አካታች የሆነው የምክክር ሂደቱ የሚጠይቃቸውን ስራዎች እየሰራን እንገኛለን። የምክክር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን ጠንካራ ስራዎች እየተሰሩ ነው። አገራዊ ምክክሩ በተናጠል ሳይሆን በርብርብ የሚሰራ በመሆኑ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋራ በመሆን ስኬታማና ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን እየሰራን ነው ብለዋል። የአገራዊ ምክክሩ ዋና ዓላማ አገራዊ መግባባትን መፍጠር በመሆኑ ሁለቱም ምክር ቤቶች ለስኬታማነቱ የበኩላቸውን ሚና ይወጣሉ ብለዋል። የምክክሩ ሂደት አሳታፊ፣ ግልጽና ነጻ እንዲሆን የሚጠበቅባቸውን እንደሚወጡም ጠቁመዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጸሃፊ ዶክተር ራሔል ባፌ እንደገለጹት፤ በጋራ ለአገራዊ ምክክሩ



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

ዶክተር ዓለሙ ስሜ

ውይይት ማድረግ መቻሉ ለምክክሩ ከፍተኛ ፋይዳ አለው። አገራዊ ምክክሩን አስመልክቶ ሁለቱ ምክር ቤቶች ለአገር ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ያደረጉት ጥምረት ዘላቂ እንዲሆን ስራዎች ይሰራሉ። ሀገራዊ ምክክሩም የታለመለትን ግብ እንዲመታ ምክር ቤቱ የሚጠበቅበትን ለመወጣት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለውጡ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በጽናት እየተሻገረ በወሳኝ ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ይገኛል!

በሕዝባዊ እንቢተኝነት የተጀመረው የአገራችን የለውጥ ንቅናቄ በየዕለቱ በሚያጋጥሙ ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ እያለፈ ከፍ ወዳለ ታሪካዊ ምዕራፍ እየተሸጋገረ፤ ራሱን በጠንካራ መሰረት ላይ የሚያዋቅርበትንና ሕዝባዊ መተማመን የሚፈጥርበትንም አቅም እየገነባ ይገኛል።

የለውጥ ኃይሉ ገና ከጅምሩ አገራዊ የለውጥ ንቅናቄው ሊያጋጥመው የሚችለውን ፈተናና ፈተናውን በጽናት ታግሎ ማሸነፍ የሚያስችል ዝግጁነት እና ቁርጠኝነት መፍጠሩ ለውጡ ለደረሰበት ታሪካዊ ምእራፍ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

የለውጥ ኃይሉን ላይ ገና ከጠዋቱ የስም ማጥፋት እና የመከፋፈል ዘመቻዎች፤ የአደባባይ የግድያ ሙከራዎች፤ ሕዝብን በሕዝብ ላይ በዘርና በሃይማኖት የማነሳሳት እኩይ ሴራዎች፤ ከዛም ባለፈ የለየለት ጦርነት ፈተናዎች አጋጥመውታል።

ፈተናዎቹ እንደ አገር የለውጥ ኃይሉን ብቻ ሳይሆን መላውን ለውጥ ናፋቂ /ፈላጊ ሕዝባችንን የፈተነ፤ እንደ ሕዝብም ሕዝባችንን ብዙ ዋጋ ያስከፈለ ነው። በአገሪቱ ታሪክም ውስጥ አገሪቱ በዚህ ደረጃ የተፈተነችበት ጊዜ መኖሩን ጠያቂዎች እንዲበራከቱ አድርጓል።

በአንድ በኩል አሸባሪው ሕወሓትና የእሱ አስተሳሰብ ሰለባ የሆኑ ቡድኖችና ኃይሎች፤ በሌላ በኩል እነሱን ባንዳ አድርገው በመጠቀም ለዘመናት አልሳካ ያላቸውን የጥፋት ተልእኮ ለማሳካት ከፍ ባለ መነሳሳት ታሪካዊ ጠላቶቻችን በብዙ ፈተናዎች ተገዳድረውናል።

አገሪቱ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያላትን ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ ለብሄራዊ ጥቅማቸው ስኬት የተንቀሳቀሱ አገራትና ኃይሎች በአደባባይ መርህ አልባ በሆነ እና ዓለም አቀፍ ህጎችን በሚገዳደር መንገድ ለውጡንና የለውጥ ኃይሉን ለማደናቀፍ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል።

ግልጽ በሆነ አገር የማፍረስ ተልዕኮ የተንቀሳቀሰው አሸባሪው ሕወሓት "አገርን ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን "በሚለው የሄደበት የጥፋት መንገድ የአገርን ህልውና ሳይቀር ስጋት ውስጥ የሚከት ደረጃ ላይ ደርሶም ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ኢትዮጵያና ስለሕዝቦቿ የነበረው የቀደመ ትርክት ተቀይሮ፤ ኢትዮጵያ እንደ አገር የመዝለቋ እውነታ ጥያቄ ውስጥ የገባበበት፤ ይህም የዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀን አጀንዳ ሆኖ ለወራት የዘለቀበት እውነታም ተፈጥሮ ነበር።

በዚህ ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈው የለውጥ ኃይሉና መላው ሕዝባችን እያንዳንዷን ፈተና በፅናት በመጋፈጥ፤ ሊከፈል የሚችለውን ሁሉ ዋጋ በመክፈል ለውጡ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ጠብቆ እንዲቀጥል አድርጓል።

አንዳንዱ ሕይወቱን፤ አንዳንዱ አካሉን፤ አንዳንዱ ተስፋውን፤ አንዳንዱ ሀብት ንብረቱን ... ሁሉም ለውጡ በጠየቀው መጠን ባለው ነገር ተፈትኖ ያለውን ነገር ሰጥቷል። በዚህ የለውጥ ኃይልነቱን ብቻ ሳይሆን ለለውጡ ያለውን ባለቤትነት በተጨባጭ አሳይቷል።

አንዳንዱ ለአገር አፍራሽ ፕሮፓጋንዳዎች እና አሉባልታዎች ጆሮውን በመንፈግ ፤አንዳንዱ ለለውጡና ለለውጡ አስተሳሰቦች ራሱን ተገዥ/ታማኝ በማድረግ ፤ አንዳንዱ ከጠላት ሴራ ራሱን ታድጎ ሌሎችን በመታደግ ለውጡ የራሱ መሆኑን በተግባር አሳይቷል።

ሕዝባችንም እንደ ህዝብ ጠላቶቻችን የፈጠሩብንን የጥላቻ፣ የርስ በርስ ግጭትና የመበተን፤ የኑሮ ውድነትና የራስ ወዳድነት ፈተናዎች በትዕግስት፣ በማስተዋል እና በሆደ ሰፊነት በማለፍ ብዙ ዋጋ ለከፈለለት ለውጥ ያለውን አጋርነት አሳይቷል። ለውጡ ጠንካራ መሰረት ላይ እንዲቆም ራሱን አቅም አድርጎ ሰጥቷል።

በዚህ ሁሉ መስዋዕትነት የተገነባው አገራዊ የለውጥ ጉዟችን በርግጥም ከትናት ዛሬ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ ስለመገኘቱ የዓባይ ግድብ የደረሰበት የግንባታ ደረጃና፤ ኤሌትሪክ የማመንጨት ስኬቱ አንዱ ማሳያ ነው።

የጸጥታ ተቋማት የሪፎርም ፕሮግራሞችና እያስገኙት ያለው ተጨባጭ ውጤት፤ ውጤቱ አገርን እንደ አገር ከማስቀጠል ባለፈ በቀጣይ የዜጎችን የእለት ተእለት ሕይወት ደህንነት አስተመማኝ ከማድረግ አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ወሳኝ ነው ።

ራስን በምግብ እህል ለመቻል በሚደረገው ጥረት በስንዴ ምርት ላይ እየታየ ያለው አገራዊ ስኬት ዓለም አቀፋዊ አድናቆት ማግኘቱ፤ በአትክልትናፍራፍሬ እና በአረንጓዴ አሻራ እየተመዘገበ ያለው ውጤትና በኤክስፖርት ዘርፍ የተገኘው አበረታችና ጅምር ውጤት ለውጡ በየጊዜው በአዳዲስ የታሪክ ምዕራፎች ውስጥ እያለፈና ፍሬ እያፈራ መሆኑን ያመላከተ ነው።

ከሁሉም በላይ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ የነበረው አገረ መንግስቱ አስተማማኝ በሆነ መሰረት ላይ የማረፉ፤ በቀጣይ አገርን እንደ አገር በቀላሉ ሊያንገጫግጭ የሚችል ነገር ስለ አለመኖሩ ማስተማመኛ የሚሆን ብሄራዊ አቅም መፈጠሩ ለውጡ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በጽናት ተሻግሮ ወሳኝ ታሪካዊ ምእራፍ ውስጥ ስለመገኘቱ ተጨባጭ ማሳያ ነው!

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## የኃያላኑ ጉሮሮ ለጉሮሮ ትንቅንቅና አንድምታው

ግርማ መንግሥቴ

የአሁኑ ዘመን የሃያላኑ አገራት የጉሮሮ ለጉሮሮ ትንቅንቅ በተለይ ሶስት አገራትን ይመለከታል። ሩሲያ እና ቻይና በአንድ በኩል፤ አሜሪካ እና ምእራቡ (አንዳንዶቹ ወጣ ገባም እያሉ ቢሆንም) በሌላኛውና ተቃራኒው ጫፍ። ለምን? ጥያቄው ይሄው ነውና በቀጥታ ወደ እሱው እንሂድ።

ሶቪየት ህብረት "ፈራረሰች" (ቃሉ በዚህ አይነት መልኩ እንዲገለፅ የምእራቡ አለም ሚዲያ የመሪነቱን ሚና ተጫውቷል) ከመባሉ በፊት "የዓለም ፖሊሶች ነን" የሚሉት ሁለቱ ነበሩ፤ ሪሲያና አሜሪካ። ሌላው የእነሱ ጀሌ ነበር፤ በወቅቱ ቻይና በከፋ ድህነት ውስጥ ነበረች።

ሶቪየት ህብረት "ፈራረሰች" ከተባለ በኋላ ያ ሁለትነት ቀረና ብቸኛዋ የዓለም ፖሊስ አሜሪካ ሆነች። በቃ። ሌላው፣ በተለይም ምእራቡ ለሷ መገበር ስራው ሆነ። የዓለም አቀፍ ተቋማቱ መርህም ያልተፃፈውን ሕግ ከማክበርና የአሜሪካን እስትንፋስ ከማስተጋባት፣ ከማክበር፣ ማፅደቅና አጨብጭቦ ወደ ተግባር ከመሸኘት ያለፈ ስራ አልነበራቸውም።

የሷን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከማስፈፀም ያለፈ ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም። ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ አለም በአሜሪካ መዳፍ ስር ተጠቃልላ ገባች። የሚጨመቀው እየተጨመቀ፤ የሚጨበጠውም እየተጨበጠ በአሜሪካ እዚህ ተደረሰ። አሁንስ?

አሁን ያለው ሁኔታ የቻይናና ሩሲያ ፍቅር ከፍ ያለ ደረጃ የደረሰበት፤ ግንኙነታቸው ጣራ የነካት፤ በንግድ፣ በዲፕሎማሲ፣ በሰላምና ደህንነት ... አንዱን ካንዱ መለየት በሚያስቸግር ሁኔታ አንድ የሆኑበትና በአንድ አካል የበላይነት ተጠፍሮ የቆየውን የዓለም የበላይነት በማስለቀቅ (ባለሙያዎቹ "Beijing and Moscow as one of pragmatism and based on "balancing" against "U.S." ይሉታል) የአለማችንን የኃይል ሚዛን ለማስጠበቅ መንቀሳቀስ ጀምረዋል።

እርግጥ ነው ጉዳዩን በጥቅል እናንሳው እንጂ ትንቅንቁ፤ ጉሮሮ ለጉሮሮ የመያያዙ ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ቀዝቃዛው ጦርነት ነው እየተደገመ ያለው የሚሉ ወገኖች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ፤ በእነዚህ ኃያላን መካከል ያለው እሰጣገባ መልኩ አንድ አይደለም፤ መገለጫውም የትየለሌ ነው።

የቻይና ሳይታሰብ ከተፍ ማለት፤ በኢኮኖሚ፣ ወታደራዊ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ .... ተገዳዳሪ ሆኖ መገኘት፤ ከሁሉም በላይ በአሜሪካ የዝንጋኤ ወቅት ሰርስራ ወደ አፍሪካ መግባቷና በአህጉሪቱ ከሚገኙ አገራት ከ46 በላይ በሆኑት ቤተሰባዊነቷን ማጠናከሯ ... ዛሬ ለአሜሪካ የእግር እሳት በመሆን እያንገበገባት ነው ።

የተከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍላ አፍሪካን ከቻይና መንጠቅ፣ ወይንም አፍሪካን መልሳ ወደ ራሷ ጉያ

**የቻይና ሳይታሰብ ከተፍ ማለት፤ በኢኮኖሚ፣ ወታደራዊ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ .... ተገዳዳሪ ሆኖ መገኘት፤ ከሁሉም በላይ በአሜሪካ የዝንጋኤ ወቅት ሰርስራ ወደ አፍሪካ መግባቷና በአህጉሪቱ ከሚገኙ አገራት ከ46 በላይ በሆኑት ቤተሰባዊነቷን ማጠናከሯ ... ዛሬ ለአሜሪካ የእግር እሳት በመሆን እያንገበገባት ነው**

ለመክተትና መሪዎቿን ተነስ፣ ቁጭ በል .... ለማለት እየቧጠጠች ያለችው ገደል በቀላሉ የሚታይ፣ የሚዳሰስ፣ የሚሰላ... አይደለም።

የሚያሳዝነው ግን ሁለቱ ዝሆኖች ሲጣሉ ተጎጂው ሳሩ መሆኑ ነው። እነሱማ ይፈራራሉና እስካሁን ከቃላት ጦርነት አልፈው ጦር ሲማዘዙ አልታዩም። በእጅ አዙር ግን ...።

### የአገራቱ ወታደራዊ ኃይል

በአሁኑ ሰአት ቻይና በአጠቃላይ 3.4 ሚሊዮን የጦር ኃይል (ከአጠቃላይ ህዝቡ 0.2 በመቶው) ሲኖራት፤ ከዚህ ውስጥ 2.1ዱ (በዚህ ቁጥር ከአለም አንደኛ ናት) በቀጥታ ውጊያ ላይ መሳተፍ የሚችል (active)፤ 70 ሰርጓጅ መርከቦች (ሩሲያ 60 ነው ያላት)... አመታዊው የመከላከያ በጀቷም $178 ቢሊዮን ነው። የሩሲያስ?

የCIA ሰነድ (CIA Factbook፣ ጁን 29, 2022) እንደሚያመለክተው ሩሲያ 850,000 ተዋጊ ኃይል (active)፤ 300,000 የምድር ኃይል፤ 40,000 አየር ወለድ፤ 150,000 ባህር ኃይል፤ 160,000 aerospace forces (አየር ኃይል)፤ 70,000 "ሮኬት ተኳሾች" (strategic rocket forces) አሏት። ገፃችን ውስን በመሆኑ ወደ መሳሪያዎቿ አልገባንም።

ይህ የድሮው ሳይሆን የአሁኑ ዘመን የሁለቱ ወዳጅ አገራት ጡንቻ ነው። ይህንን ጡንቻ በማስተባበር ነው በተሳሳተ መንገድ በዓለም ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶና ፀንቶ የኖረውን የአሜሪካንን የበላይነት (ወታደራዊ የበላይነት፣ ጣልቃ ገብነት፣ ጉልበተኛነት) ርእዮት ("of militarism, interventionism and the forcible imposition of U.S. values on other countries.") ከስሩ መንግሎ ለመጣልና በምትኩ የሁሉንም እኩልነት የምታስተናግድ ዓለም ለመፍጠር እየተንቀሳቀሱ ያሉት።

ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ አልሞት ባይ ተጋዳይነት ካልሆነ በስተቀር የአሜሪካ የበላይነት እንደ ሆነ ከተወሰደ ቆይቷል። በጦርነቱም ከሆነ ሩሲያ በኒውክሌር ጦር መሳሪያዋ የአሜሪካንን ሚሳኤሎች ጭጭጭ ምጭጭጭ ማድረግ የሚያቅታት ምንም ነገር የለም። በመሆኑም መፍትሄም አሜሪካ እጅ ወደ መስጠትና አብሮ መስራት መምጣት፤ ፌዙን በማቆም፣ "የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዬ ነው" የምትለው የሷ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የራሷ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ብቻ መሆኑን መገንዘብና ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ መመለስ ብቻ ነው።

ከሲኖ-አሜሪካ ጋር በተያያዘ ናሳ የእስከዛሬው አካሄዴን ቀይሬያለሁ፤ የመጪው ዘመን የዓለማችን ስጋት የሆነችውን፤ የቻይናን እንቅስቃሴ ለመግታት ከተለመደው ክትትሌና አካሄዴ ወጥቻለሁ። ትኩረቴንም ቴክኖሎጂ(ዋ) ላይ አድርጌያለሁ፤ ለዚህም ከፍተኛ በጀት መመደብ ብቻ ሳይሆን በቂ የሰው ኃይልም አዘጋጅቻለሁ .... ሲል ሰሞኑን የለቀቀውን መግለጫም እዚሁ ላይ ከስሩ አስምረንበት ልናልፍ የሚገባን ጉዳይ ነው። (ይህ በቻይና በኩል እንዴት ይታያል? የሚለውን ለሌላ ጊዜ እናቆየው።)

የቻይና ወደ አፍሪካ ዘልቆ መግባትን በተመለከተም፤ ባልተቋረጠ መልኩ ቻይና አፍሪካን በእዳ ትብትብ አድርጋ በመያዝ ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ እየገዛች ነው የሚለው የአሜሪካ ክስ በሁሉም በሚያስብል ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ አይመስልም። እንደውም ያለው እውነታ የሚያሳየው "ከቻይና ጋር ወደፊት!!!" መሆኑን ነው።

ይህ ደግሞ አሜሪካንን ክፉኛ አስቆጥቷታል ብቻ ሳይሆን ራሷን እንድትስት ሁሉ ያደረጋት እስኪመስል ድረስ አበሳጭቷታል። በተለይ አፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የአፍሪካ አገራት "ለፀረ-ሩሲያ አቋሜ ኑ ከጎኔ ቁሙ" ለሚለው ጥሪዋ ምላሽ አለመስጠታቸው በብሊንከን አማካኝነት ቤት ለቤት እየሄደች እንደ ሁኔታው (በማስፈራራት ወይም በማባበል ...) በመነጋገር ላይ መገኘቷ እንዳለ ሆኖ ብሊንከን ራሳቸው ለቻይና እዚህ መድረስ ስህተቱ የኛ ነው እስኪሉ ድረስ ሁሉ እንዲሄዱ አድርጓቸዋልና ጉዳዩ የዋዛ አይደለም። በመሆኑም በምትችለው ሁሉ የምትችለውን እያደረገች ትገኛለች። (ዝርዝሩ ብዙ ነው።) ይሳካል፤ አይሳካም ... ወደ ፊት የሚታይ ነው የሚሆነው።

ቻይናና ሩሲያን በተመለከተ የሚወጡ ትንተናዎች እንደሚያሳዩት ሁለቱ የሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮች በርካታ ሲሆኑ ከሁሉም ቀዳሚው ሁለቱም ራሳቸውን ችለው የኖሩና ረጅም ዘመን የመንግስትነት ልምድ ያላቸው መሆናቸው (autonomous countries with strong state traditions) ነው። አንድነታቸው ከዚህ ይጀምራል። ሌላውን ከወቅቱ ሁኔታ እየተነሳ አንባቢ ሊሞላው ይችላል።

በአጠቃላይ ትንቅንቁ ቀጥሏል። (የ'ኛን፤ በእኛ ላይ እየተደረገ ያለውን ዝም ነው) ጦርነቱ ዩክሬን ላይ ተጀምሯል። ታይዋንን በተመለከተ እየተንደረደሩ መሆኑን እንጂ ስለ መጀመራቸው/አለመጀመራቸው የታወቀ ነገር የለም። በአፍሪካ ምድር የቻይናና ሩሲያ ፖሊሲ ነው የሚቀይረው? አፍሪካ ወደ ኋላ ትመለሳለች? ወይስ፣ አሜሪካ ነች ፖሊሲዋን ወደ ዘመኑ አፎት እንዲገባ ለማድረግ የምትጥረው የሚለው፤ የመጀመሪያውና ሁለተኛው የሚሆን ባይመስልም አጠቃላይ ውጤቱን ግን ወደፊት አብረን የምናየው ይሆናል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

# በሸማች ማህበሩ የተደረገው «ሪፎርም» ያስነሳው ውዝግብ

ሙሉቀን ታደገ

የዛሬው «የፍረዱኝ አምድ ዝግጅታችን በአዲስ አበባ ከተማ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ በተለምዶ አራት ኪሎ እየተባለ ወደ ሚጠራው አካባቢ ይወስደናል። አቤቱታ አቅራቢዎች በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ዘጠኝ በሚገኘው የእፎይታ ሸማቾች ማህበር አባል የሆኑት አቶ ዘካሪያስ ሄራኖ የተባሉ ግለሰብ እና ሌሎች ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የእፎይታ ሸማቾች ማህበር አባላት እንዲሁም አንዳንድ የማህበሩ ሰራተኞች ናቸው።


ከዚህ ቀደም የእፎይታ ሸማቾች ማህበርን በቦርድ አመራርነት ሲያገለግሉ የቆዩ ሰዎች ማህበሩን ከመመሪያ እና አሰራር ውጭ እንደፈለጉ በመመዝበራቸው ምክንያት 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት እንዳለ ከክፍለ በመጡ የኦዲት ባለሙያዎች ባወጡት ሪፖርት ተመላክቷል። የቦርድ አመራሮቹ ይህን ያህል ገንዘብ ማጉደላቸው በኦዲተሮች ተረጋግጦ ሳለ እነኝህ አመራሮች ለጎደለው ገንዘብ ተጠያቂ መሆን ሲገባቸው ከህግ እና ስርዓት ባፈነገጠ መልኩ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ የማህበሩ የቦርድ አመራር ሆነው እንዲመረጡ ተደርጓል። «ይህ ውሳኔ ማህበሩን እና አባላቶቹን ለከፋ ለችግር እንዲጋለጡ እያደረገ ነው » ሲሉ አቶ ዘካሪያስ ሄራኖ እና ሌሎች የእፎይታ ሸማች ማህበሩ አባላት እንዲሁም ሰራተኞች ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤቱታቸውን አቅርበዋል። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ የደረሰበትን ሙሉ የምርመራ ውጤቱን እነሆ ብሏል። መልካም ንባብ።

### የቅሬታው መነሻ- ከአቶ ዘካሪያስ ሄራኖ አንደበት፡-

እንደ አቶ ዘካሪያስ ሄራኖ ገለጻ፤ በዚህ ወረዳ የሚገኙ ነዋሪዎች በመላው አገሪቱ እንደሚኖሩ ኢትዮጵያዊን ሁሉ የኑሮ ውድነትን በመከላከል ጤናማ ኑሮን ለመምራት በማሰብ በ2000 ዓ.ም የእፎይታ የሸማቾች ማኀበር የተባለ የህብረት ስራ ማህበር መሰረቱ። ማህበሩ ከ1ሺህ 800 በላይ አባላትን ይዞ የተመሰረተ ቢሆንም አሁን ላይ ግን ማህበሩ ከ2ሺህ 500 በላይ አባላትን አቅፎ ይዟል። አቶ ዘካሪያስ ሄራኖ በዚህ ማህበር አባል ሲሆኑ የአክሲዮን ድርሻም አላቸው።

ማህበሩ ተጠሪነቱ ለአባላቱ ነው የሚሉት አቶ ዘካሪያስ፤ ችግር ሲፈጠር የወረዳው ዋና ስራ አስፈጻሚ ችግሩን ተከታትለው መፍትሄ እንደሚያሰጡት ይናገራሉ። ማህበሩ ከዚህ ቀደም 2,000,000 ተንቀሳቃሽ ካፒታል እና 8 መቶ ሺህ ብር ለትርፍ ክፍፍል የተቀመጠ ካፒታል ነበረው። ማህበሩ ከተመሰረተበት ዓላማ አንጻር ለተወሰኑ ጊዜያት ትርፋማ የነበረ እና ለአባላቶቹም የትርፍ ክፍፍል እስከማድረግ ደርሶ ነበረ። ይሁን እንጂ አሁን ላይ የማህበሩ የቦርድ አመራሮች እና በማህበሩ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች በሚያደርጉት «አይን ያወጣ ዝርፊያ እና ሌብነት» እንዲሁም የአየር ባየር ንግድ ሳቢያ ማህበሩ ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጉን ይናገራሉ።

በ2013 ዓ.ም አቶ ዘካሪያስን ጨምሮ በርካታ የማህበሩ አባላት እና ሰራተኞች በማህበሩ የሚስተዋሉ ያልተገቡ አሰራሮችን በማየታቸው ማህበሩ ኦዲት እንዲደረግላቸው ይጠይቃሉ። በዚህም መሰረት ከአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ጽ/ቤት ኦዲት ቡድን የመጡ የኦዲተሮች የማህበሩን ከሐምሌ 1 ቀን 2012 እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የአንድ ዓመት አጠቃላይ ወጪ እና ገቢ የኦዲት ምርመራ


አራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ጽ/ቤት

ኦዲት ቡድን

Arada Sub-city Co-operatives Office

Co-operatives organizing – Audit Service Team

ቁጥር አ/ክ/ህ/ስ/ጽ/ቤ/ት/ኦ/ቡ.................../14

ቀን 18 / 9 /2014ዓ.ም

ለወረዳ 9 እፎይታ ሸማች

ኃላ/የተ/የህ/ስራ ማህበር

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የአራዳ ክፍለ ከተማ ኅብረት ሥራ ጽ/ቤት ኦዲት ቡድን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 50 መሠረት በማድረግ ከሐምሌ1/2012 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2013ዓ.ም የአንድ ዓመት ሂሳብ መርምረን የተገኘው ውጤት የያዘ 11 ገጽ ያለው የኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል።

ማህበሩ ሊያስተካክላቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ሁሉ በሪፖርቱ ውስጥ የተመለከቱ ስለሆነ ተገቢ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስዱ እናሳስባለን።

በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 50 መሠረት ሪፖርቱ ለማህበሩ ከደረሰበት ጊዜ ጀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይህ ሪፖርት ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብና እንዲገለጽ እናሳስባለን

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር

- ለህ/ሥ/ኦ/ቡድን

አራዳ ክፍለ ከተማ

ስልክ ቁጥር +251-11126-65-13

ያደርጋሉ። በዚህ የኦዲት ምርመራ በማህበሩ 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት መኖሩን ታወቀ።

ይህ በእንዲህ እያለ በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው አባላት በተገኙበት ሰኔ 19/2014 ዓ.ም በወረዳ ዘጠኝ ስብሰባ ተካሄደ። በሸማች ማህበሩ ከፍተኛ የገንዘብ ብክነትን መኖሩን የተገነዘቡት የማህበሩ አባላት እና ሰራተኞች ይህ የኦዲት ጉድለት እንዲከሰት ያደረጉ የማህበሩ ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ይጠየቁ ሲሉ በስብሰባው ላይ ሃሳብ ቢያነሱም ለጥያቄአቸው ምላሽ የሚሰጥ ሰው ማግኘት ሳይችሉ መቅረታቸውን አቶ ዘካሪያስ ይናገራሉ።

የሸማች ማህበሩ ቅሬታ አቅርበው ኦዲተር ከክፍለ ከተማው ይመጣል ተብሎ በሰኔ 19/2014 ዓ.ም ቀጠሮ ያስያዙት ቅሬታ አቅራቢዎች ሆነው ሳለ በቀኑ በተካሄደው ስብሳባ ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡ የማህበሩ አባላት እና ሰራተኞችን በማዳመጥ ተገቢውን መልስ ከመስጠት ይልቅ በስብሰባው ጉድለት የተገኘባቸው እና አቤቱታ የቀረበባቸው አመራሮች የስብሰባ አጀንዳውን ወደ ጎን በመተው የራሳቸውን አጀንዳ ለተሰብሳቢው በማቅረብ ራሳቸው ጠያቂ፤ ራሳቸው መላሽ ሆነው አረፉት ሲሉ አቶ ዘካሪያስ ያስረዳሉ።

መጀመሪያውኑ ስብሰባ መካሄድ ያለበት ምልዓተ ጉባኤ ሲሟላ ነው የሚሉት አቶ ዘካሪያስ፤ ከ2 ሺህ በላይ ማህበሩ አባላት ያሉት ቢሆንም በስብሰባው የተገኘው አጠቃላይ የሰው ብዛት ከ70 አይበልጡም፤ ከእነኝህ መካከልም አብዛኛዎቹ የራሳቸው የቅጥር ሰራተኞች መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ይህን ተከትሎ ምዕላተ ጉባኤው ሳይሟላ ስብሰባው መደረግ የለበትም! ውሳኔ ማስተላፍም ተገቢ እና ህጋዊ አይደለም! ነገር ግን አመታዊ የማህበሩን ሪፖርት እወቁ የምትሉ ከሆነ አውቀን እንሄዳለን። ይሁን እንጂ ምዕላተ ጉባኤው ሳይሟላ የሚጸድቅ፣ የሚሻር እና የሚሻሻል ነገር መኖር የለበትም የሚል ቅሬታ ለስብሰባው አዘጋጆች ቢያቀርቡም የስብሰባ አዘጋጆች ከማዳመጥ ይልቅ የሙብት ጥያቄ ባነሱ የማህበሩ አባላት ላይ ማስፈራሪያ እና ዛቻ እንደደረሰባቸው አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ።

በዚህም አቶ ዘካሪያስ እና ሌሎች ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያጣል። የማህበሩ አባላት እና ሰራተኞችን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ስብሰባውን ያዘጋጁት ሰዎች «እኛ የመጣነው በሌሎች ወረዳዎች በሚገኙ ማህበራት ላይ እንዳደረግነው ሁሉ በዚህም ወረዳ በሚገኘው የሸማች ማህበር ሪፎርም ለማድረግ ነው።» ይሏቸዋል። ይህን ተከትሎ ሪፎርሙ ምን እንደሆነ እንስማው፤ ነገር ግን ሌላ ውሳኔ ግን ምዕላተ ጉባኤው ሳይሟላ መወሰን አትችሉም ሲሉ በድጋሚ ለሰብሳቢዎች ሊያመላክቱ መሞከራቸውን ነገር ግን ለችግራቸው ጆሮ ሊሰጥ የሚችል ማግኘት አለመቻላቸውን ይገልጻሉ።

ይህን ተከትሎ የማህበሩ አባላት ቢያንስ ቢያንስ 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት እንዲፈጠር ያደረጉ አካላት ይጠየቁልን? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። ስብሰባውን የሚመራው አካል ጉድለት እንዲፈጠር ያደረገን አካል ከመጠየቅ ይልቅ የተፈጠረው ጉድለት በሪፎርሙ ይስተካከላል በማለት አድበስብሶ ማለፉን እና ዛሬ የምንወስነውን ውሳኔ በጭብጨባ ማጽደቅ አለባችሁ ብሎ እንዲያጨበጭቡ መገደዳቸውን ያስታውሳሉ።

እንደ አቶ ዘካሪያስ ገለጻ፤ ለስብሰባ የተጠሩት አርባ የማህበሩ አባላት ብቻ ናቸው። ምክንቱም ሌሎች የማህበሩ አባላት ቢገኙ ችግር ይፈጥራሉ፤ ይቃወሙናል በሚል ነው። ይሁን እንጂ የተገኙት እነኝህ አርባዎቹም በራሳቸው በፈቃደኝነት ሪፖርቱን ተቀብለው ሪፎርሙን ተቀብለው የኮሚቴዎችን ምርጫ አላጸደቁም።

ሰብሳቢዎችም የማህበሩን አባላት ፍላጎት ወደጎን በመተው ሪፖርቱን በጭብጨባ ካጸደቁ በኋላ ኮሚቴ ምርጫ ይካሂድ ተባለ። ይህን ተከትሎ ጠቅላላ ጉባኤ ባልተገኘበት ምርጫ ማካሄድ አይቻልም ምክንቱም እዚህ የሚገኘው የማህበሩ አባል ከ2 ሺህ ስምንት መቶ መካከል ስብሰባው ላይ የተገኘው አርባ አይሞላም። ይህ በሆነበት የኮሚቴ ምርጫ መካሄድ የለበትም የሚል ተቃውሞ ማንሳታቸውን ይናጋራሉ። ሪፖርቱን ሰምተናል፤ በዚህም ጉድለቱን ሰምተናል። ይህን ጉድለት ያደረሱ ሰዎች ሳይጠየቁ በፊት ሌላ ኮሚቴ መመረጥ የለበትም ቢባሉም ጥያቄ አናስተናግድም በማለት የኮሚቴ ምርጫ አንዲካሄድ ተደርጓል።

ምርጫውን የሚያካሂዱ ሰዎች ደግሞ ከክፍለ ከተማ የመጡ ሰዎች ናቸው። ምርጫውን ያካሄዱት ሰዎች ምንም ስለማህበሩ የማይመለከታቸው ሰዎች ናቸው። የማህበራት ማደራጃዋ አንድ ቆጣሪ በመሆን ምርጫው እንዲካሄድ ተደረገ፡፤ ምርጫው ሲካሄድ 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት ተጠየቂ መሆን የሚገባቸው ሰዎች እንደገና ተመረጡ። ከዚህ በፊት የነበሩ እና በስራ ዘመናቸው 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት ያጎደሉ ሰዎች በምርጫው እንኳን መካተት የለባቸውም የሚለውን ለመናገር እድሉን ሳናገኝ ቀረን ። በዚህም መሰረት ራሳቸው መራጭ፣ አስመራጭ እና ራሳቸው አጽዳቂ፣ ራሳቸው ቆጣሪ በመሆን ከክፍለ ከተማ ሪፎርም ተብሎ የመጡ ሰዎች ይህን አይነት ውሳኔ አስተላልፈው ሂደዋል።

ቅሬታ አቅራቢው አቶ ዘካርያስ እንደተናገሩት፤ 649 ሺህ 645 ብር ጉድለት እየታየ እና በርካታ በማህበሩ ውስጥ ያልተጣሩ እና የተዝረከረኩ እንዲሁም የባከኑ ሃብቶች እያሉ ተጠያቂ መሆን የሚገባቸውን ሰዎች መልሶ የቦርድ አባል አድርጎ መመረጥ የለባቸውም። ለጉድለቱ ተጠያቂው ሳይታወቅ ማንን ተጠያቂ በማድረግ ነው ምርጫ የሚደረገው? አይደለም 649 ሺህ 645 ብር ያህል ብር ይቅርና የህዝብ ንብረት እስከሆነ ድረስ አንድ ብር ጉድለት ካለ ያጎደለው ሰው ሊጠየቅ ይገባ ነበር። ሪፎርሙስ የጎደለውን ራሱ ያስተካክለዋል የሚባለው ሪፎርሙ ከየት አምጥቶ ነው ጉድለቱን የሚያስተካክለው? ሲሉ ይጠይቃሉ።

ሌላው አቤቱታ አቅራቢ ስማቸው እንዲጠቀስ አልፈለጉም። እኝህ አቤቱታ አቅራቢ በማህበሩ ሰራተኛ እና የማህበሩ ባለአክሲዮን አባል ናቸው። እንደ አቤቱታ አቅራቢው በየጊዜው የሚበላሹ የማህበሩ ሸቀጦች አሉ። ለእነዚህ ሸቀጦች መበላሸት ዋና ምክንያት አመራሮች ናቸው። ምክንያቱም ለመስረቅ ይመቻቸው ዘንድ ሆነ ብለው የሚያደርጉት መሆኑን ይናገራሉ። መጋዘን ውስጥ ቢገባም በርካታ የተባላሹ እቃዎች እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ሌላው አመራሮች የተጠቀሙት የመዝረፊያ ስልት ደግሞ ለመከላከያ፣ ለአባይ ግድብ እና መሰል አገራዊ ለሆኑ ግዳጆች በሚል ሰበብ መሆኑን አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ። በዚህም ያለ ማህበሩ አባላት እውቅና ከመቶ ሺህዎች እስከ ሚሊዮን የሚደርሱ ገንዘቦችን በእርዳታ ስም እየተዘረፉ እንዲወጡ ተደርጓል ይላሉ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ሌላው ደግሞ በህብረት ማህበራት ሱቆች ለአጥር እና ጣሪያ በጥገና ስም የሚወጡ ወጭዎች ናቸው። በዚህም ይሄን ያህል ቦታ 30 ሺህ፤ ይሄን ያህል ቦታ 20 ሺህ ብር አውጥተን አጥር አጥረናል ወዘተ እያሉ የማህበሩን ገንዘብ ይመዘብራሉ። ይሄን እና መሰል አይነት ምክንያት አልባ ወጭ ሲደረግ ለምን ካልኩ ምን አገባህ ከፈለክ ስራህን መልቀቅ ትችላለህ መባላቸውን አቤቱታ አቅራቢው ይገልጻሉ።

እንዲሁም ለህዝቡ የሚመጡ ስኳር፣ ዘይት እና መሰል ሸቀጦች ለማህበሩ አባላት በትክክል አይሸጥም። ለምሳሌ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ አንድ ነጋዴ 100 ኪሎ ስኳር እንዲወስድ ቢፈቀድለት የሸማች ማህበር አመራሩ ከነጋዴው ጋር በመመሳጠር የመጀመሪያዋን አንድ ቁጥር አራት ወይም አምስት በማድረግ 5 መቶ ወይም 4 መቶ ኪሎ ስኳር እንዲወስድ ያደርጋሉ። ነጋዴው ከተፈቀደለት መጠን በላይ ከወሰደው ስኳር የሚገኘውን ትርፍ በጋራ ይካፈላሉ።

ቅሬታ አቅራቢው እንደሚሉት፤ ሰኔ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሁሉም የማህበሩ ሰራተኛ ተሰብስቦ ነገ የሚደረገውን ምርጫ እና ውሳኔ ሂደት በጭብጨባ መደገፍ እንዳለበት መመሪያ ሲተላለፍ ነበር። በዚህም መሰረት ሰኔ 19/2014 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባ የማህበሩ አባላት ሳይገኙ እንዲያጨበጭቡ መመሪያ የተሰጣቸው ሰዎች ፊት ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ይጽደቁ የተባሉ ነገሮችን በሙሉ በጭብጨባ አጸደቁ። ነገር ግን ቅሬታ ለማቅረብ እጅ የሚያወጡ ሰዎችን ቅሬታ አልቀበልም በማለት ድምጻችንን አፈኑ።

ይሁን እንጂ እነኘህ ሰዎች አንመርጥም ቢባል ቀድመው እንዲያጨበጭቡ መመሪያ የተሰጣቸው ሰዎችን በመመደብ እና የተቃውሞ ጥያቄ ያላቸውን ሰዎች ጥያቄ ባለማስተናገድ ማህበሩን ሲዘርፉ የነበሩት ሰዎች እንደገና በአመራርነት እንዲመረጡ ተደርጓል።

በየሳምንቱ እሁድ እሁድ ማህበሩ የጎዳና ሽያጭ ያደርጋል። በዚህም ማህበሩ በየሳምንቱ ከ1ሺህ አምስት መቶ ብር በላይ ለሆነ ኪሳራ እንደሚዳረግ አቤቱታ አቅራቢው ተናግረዋል።

ሌላው ማህበሩን ለኪሳራ የዳረገው ዋናው ምክንያት የስራ አስኪያጁ በእድሜ የገፉ መሆናቸው ነው የሚሉት ቅሬታ አቅራቢው፤ ስራ አስኪያጁ መምህር የነበሩ እና በእድሜ መግፋት ምክንያት በጡረታ የተገለሉ ናቸው። ይሁን እንጂ በማን አለብኝነት ለማህበራችን ስራ አስኪያጅ ሆነው መመረጣቸውን ይናገራሉ።

ስራ አስኪያጅ ሆነው የተመረጡት ሰው አይደለም የንግድ ስራን ያህል ነገር ለመምራት ይቅራና ራሳቸውን በደንብ ተንከባክበው መዋል የማይችሉ ናቸው የሚሉት አቤቱታ አቅራቢው፤ ይሁን እጂ የቦርድ አመራሮች የማህበሩን ገንዘብ እንደፈለጉ ለመስረቅ እንዲመቻቸው በአካል የደከሙ አዛውንት ሰው ስራ አስኪያጅ በማድረግ መርጠዋል። አሁን ስራ አስኪያጅ ሆነው የተመደበው ሰው በአሁኑ ጊዜ በቤተእምነታቸው ለጸሎት ከመሄድ ውጭ ሌላ ምንም ስራ መስራት የማይችሉ መሆናቸውን አመላክተዋል።

አቤቱታ አቅራቢው እንዳሉት፤ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የማህበሩ አባል ያልሆነ ሰው በቦርድ አመራርነት ሊሰራ አይችልም። ይሁን እንጂ በወረዳ ዘጠኝ የሚገኘውን የሸማች ማህበር ህብረት ለማዘረፍ በማሰብ አቶ ታደሰ በየነ የተባሉ ግለሰብን ከመመሪያ እና የአሰራር ደንብ ውጭ በኮሚቴነት በማስቀመጥ በየወሩ ደሞዝ መክፈላቸው ይገልጻሉ።

ቅሬታና አቤቱታ አቅራቢዎቹ ሌብነት፤ የአሰራር ብልሹነት፣ የመመሪያና መተዳደሪያ ደንብ ጥሰት ነው ያሉትን አቅርበዋል። በዚህ ዙሪያስ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ምን አሉ ?

## የእፎይታ ሸማቾች ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ ምላሽ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ የእፎይታ ሸማቾች ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ዳንኤል ጸጋው አቤቱታ አቅራቢዎች ያነሷቸውን ጥያቄዎች እና ሌሎች ከዝግጅት ክፍሉ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ ይዘን ቀርበናል ።

በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 09 እፎይታ የሸማቾች ኃላ/የተ/የሀ/ስ/ማ
የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ
ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

| | 30/10/2013 ዓ/ም | 30/10/2012 ዓ/ም |
|---|---|---|
| የተጣራ ገንዘብ ከስራ እንቅስቃሴ | (646,894.28) | 685,814.43 |
| ከኢንቨስትመንት ስራ እንቅስቃሴ ገቢ እና ወጪ | | |
| መጋዘን ያለ ዕቃ መጨመር | (416,929.84) | |
| ኢንቨስትመንት | (100,000.00) | (15,000.00) |
| የእርጅና ተቀናሽ | 22,380.71 | |
| ቋሚ ዕቃ ግዢ | (13,800.00) | (230,954.21) |
| የተጣራ ገንዘብ ከኢንቨስትመንት ስራ እንቅስቃሴ | (508,349.13) | 439,860.22 |
| ከገንዘብ(ፋይናንሲንግ)እንቅስቃሴ ገቢ እና ወጪ | | |
| ተሰብሳቢ ገንዘብ መጨመር | (1,632.12) | |
| ተከፋይ ገንዘብ መጨመር | 1,266,047.40 | 72,159.13 |
| የአባላት ዕጣ/ሼር መጨመር | 750.00 | 5,550.00 |
| የትርፍ ክፍፍል ወጪ | - | - |
| የተጣራ ገንዘብ ከፋይናንስ | 1,265,165.28 | 77,709.13 |
| **ማጠቃለያ** | | |
| የተጣራ ገንዘብ ለውጥ | 109,921.87 | 517,569.35 |
| ጥሬ ገንዘብ በእጅእና በባንክ 30/10/2012ዓ.ም | 1,119,117.99 | 1,119,117.99 |
| ጥሬ ገንዘብ በእጅእና በባንክ 30/10/2013 ዓ.ም | 1,229,039.86 | 601,548.64 |

በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 09 እፎይታ የሸማቾች ኃላ/የተ/የሀ/ስ/ማ
የትርፍና ኪሳራ መግለጫ
ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

| | መግለጫ | 30/10/2013 ዓ/ም | 30/10/2012 ዓ/ም |
|---|---|---|---|
| **ገቢ** | | | |
| ሽያጭ | 15 | 16,714,830.50 | 14,974,364.18 |
| የተሸጠ የዕቃ ዋጋ | 17 | 16,381,152.24 | 13,983,357.03 |
| ያልተጣራ ትርፍ | | 333,678.26 | 991,007.15 |
| ሌሎች ገቢዎች | 16 | 9,821.30 | 7,520.20 |
| የገቢ ድምር | | 343,499.56 | 983,486.95 |
| **የአስተዳደርና አጠቃላይ ወጪዎች** | | | |
| የሽያጭ ወጪዎች | 18 | 217,334.00 | 195,868.00 |
| አጠቃላይ የአስተዳደር ወጪዎች | 19 | 773,059.84 | 575,059.18 |
| የወጪ ድምር | | 990,393.84 | 770,927.18 |
| የአመቱ የተጣራ ትርፍ | | (646,894.28) | 231,300.17 |
| **የትርፍ አደላደል** | | | |
| የመጠባበቂያ ተቀማጭ | | (135,847.80) | - |
| ያልተከፋፈለ ትርፍ | | (452,826.00) | 231,300.17 |

መጀመሪያው ለአቶ ዳንኤል ያነሳነው ጥያቄ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በእድሜ የገፉ ሆነው ሳለ ለምን የስራ አስፈጻሚ ተደረጉ? የሚል ነበር። ለተጠየቁት ጥያቄ ማብራሪያ የሰጡት ሰብሳቢው፣ ‹‹እውነት ነው ስራ አስኪያጁ በእድሜ የገፉ ነበር። ይህ የሆነው ከሪፎርሙ በፊት ነው። አሁን ላይ ማለትም ከሪፎርሙ በኋላ ግን ከነበሩበት ኃላፊነት ተነስተው የሰው ሃይል አስተዳደር እንዲሆኑ ተደርጓል ›› የሚል ነው። ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ምርመራ ክፍል የሰው ሃይል አስተዳደር ትልቅ ስራ ሆኖ ሳለ ስለምን በእኝህ አዛውንት እንዲመራ ተደረገ ? ሲል የቦርድ ሰብሳቢውን ጠይቋል። ለዚህ ምላሽ የሰጡት የቦርድ ሰብሳቢው ‹‹ አሁን ሰውየውን በሌላ ለመተካት እየሰራን ነው›› የሚል ነው።

የማህበሩ የመነሻ ከፒታል ምን ያህል ነው ? አሁንስ ምን ያህል ድርሷል ? አሁን ላይ አባሎቻችሁ ብዛት ምን ያህል ነው? በሚል ለቀረበው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ የማህበሩ መነሻ ካፒታል 57 ሺህ ነበር። አሁን ላይ በቆጠራ የተገኘ 2 ሚሊዮን 816 ሺህ 796 ብር ከ87 ሳንቲም፣ በጥሬ የተገኘ 2 ሚሊዮን 981 ሺህ 358 ብር ከ58 ሳንቲም እና ቅድመ ክፍያ 923 ሺህ ከ35 ሳንቲም ሲሆን አጠቃላይ አሁን ላይ ማህበሩ ሃብት 6 ሚሊዮን 711ሺህ 190 ከ82 ሳንቲም ነው። ይህ የተጠቀሰው አሃዝ የሸማች ማህበሩ ከዩኒየን በብድር ለመሸጥ ያመጣቸውን ንብረቶች የሚጨምር ነው። ይህንንም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ከሰነዶች ማረጋገጥ ችሏል። አሁን ላይ በእፎታ ሸማቾች ማህበር የሚገኘው የአባላት ብዛት 1 ሺህ 976 ነው ።

በአሁኑ ወቅት በኦዲተሮች እንደተረጋገጠው በሸማች ማህበሩ ገንዘብ ጉድለት መኖሩ ነው። ስለዚህ ምን ይላሉ ተብለው የተጠየቁት የቦርድ ሰብሳቢው ‹‹ምን አይነት የገንዘብ ጉድለት የለም›› ሲሉ ተናግረዋል። ይህን የቦርድ ሰብሳቢውን መልስ ተከትሎ በኦዲቲንግ ባለሙያዎች የተረጋገጠ ምን አይነት የኦዲት ጉድለት አልተገኘም ? ሲል የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በድጋሚ የቦርድ ሰብሳቢውን ጠየቀ። ዝግጅት ክፍሉ ለጠየቃቸው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት የቦርድ ሰብሳቢ ‹‹አዎ ኦዲተሮች መጥተው የማህበሩን ገንዘብ ኦዲት አድርገዋል። የኦዲት ምርመራ ውጤቱም ሃምሌ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በነበረው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተናግረዋል። የኦዲት ሪፖርቱን ከማህበሩ አባላት እኩል ሀምሌ 19 በነበረው ስብሰባ መስማታቸውን አረጋግጠዋል››።

በተለያዩ ምክንያቶች ኪሳራዎች አጋጥመው ካልሆነ በስተቀር ምንም አይነት ጉድለት የለም ያሉት የቦርድ ሰብሳቢው ተፈጥሯል የተባለው የኦዲት ሪፖርት ማህበሩን ስለማይወክል እንደገና ኦዲት እንዲረግላቸው መጠየቃቸውንም ገልጸዋል።

በጠቅላለ ጉባኤው የተገለጸው 649 ሺህ 645 ብር ያህል ጉድለት መኖሩን ነው። አንድ ነገር እንስማማ በማህበሩ ጉድለት እንዳለበት ተነጋግራችኋል ወይስ የለም ? ተብለው የተጠየቁት የቦርድ ሰብሳቢው እንደተናገሩት ‹‹ጉድለት የለም፤ ነገር ግን ኪሳራ አጋጥሟል›› ሲሉ ተናግረዋል። ይህን ተከትሎ ማህበሩ በዚህ ደረጃ እንዲከስር ያደረጉ አመራሮች ምን እርምጃ ተወሰደባቸው ? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው የቦርድ ሰብሳቢው እንደዚህ አይነት ችግር ሲያጋጥም መጀመሪያ ችግሩን ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል። የህግ ክፍተት ካለውም በህግ እንዲታይ ይደረጋል። እርሳቸው የሚመሩት የሸማች ማህበርም ችግር በገጠመው ጊዜ የማህበር አባላቱን ሰብስቦ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፊት መነጋገራቸውን ገልጸዋል።

በውይይቱ ለኪሳራው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው ተብለው ሲጠየቁም ምለሽ የሰጡት ሰብሳቢው ‹‹ለኪሳራው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ እንዳልተጠቀሰ እና ለኪሳራ ሊዳርጉ የሚችሉ የማህበሩ አመራሮች ድክመት በስፋት ተነስቷል›› ሲሉ ገልጸዋል። በዚህም መሰረት የሂሳብ ሰራተኞች የሂሳብ አመዘጋገብ እና የቆጠራ ችግር ለኪሳራው መፈጠር እንደ ዋና ምክንያት ጠቅሰዋል። ለኪሳራው ሌላኛው ምክንያት ከኮቪድ ወረርሽን ነው ያሉት የቦርድ ሰብሳቢው፤ በወረርሽኙ የሸቀጥ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ መቀዛቀዙን ይናገራሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ ማህበሩን ለኪሳራ ከዳረጉት ነገሮች መካከል አንዱ አገራዊ ግዴታዎች በዋነኛነት ያነሳሉ። ሸማቾች ማህበር ለማትረፍ ያልተቋቋመ በመሆኑም ስራ ኖረም አልኖረም አገራዊ ግዴታዎቻችንን በሙሉ ሲወጡ መቆየታቸውን ይናጋራሉ። ይህ ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ማህበሩ እየከሰረ ነው ወይ አገራዊ ኃላፊነቶችን መወጣት ያለበት ሲል ይጠይቃል። ሰብሳቢውም ኪሳራ ላይ መሆናቸውን ቆይተው እንደተገነዘቡት ጠቁመዋል።

የእፎይታ ሸማቾች ማህበር በየሳምንቱ የጎዳና ላይ ንግድ እንደሚያካሄድ እና በዚህም በየሳምንቱ ኪሳራ እያጋጠማው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ ተብለው የተጠየቁት አቶ ዳንኤል፤ የተባለው ነገር እውነት መሆኑን ጠቁመው፤ ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት መንግስት ገበያን ለማረጋጋት ሸቀጦችን በቅናሽ ዋጋ እንዲሸጡ ትዕዛዝ በማስተላለፉ መሆኑን አመላክተዋል።

ማህበሩ የነበረውን ካፒታል ስለጨረሰ ከአዲስ ብድር እና ቁጠባ ተቋም መበደራችሁን አቤቱታ አቅራቢዎች ይናገራሉ ስለዚህ ምን ይላሉ ? ስንል አቶ ዳንኤልን ጠይቀን ነበር። አቶ ዳንኤልም በአቤቱታ አቅራቢዎች የተነሳው ክስ ሃሰት መሆኑን ጠቁመዋል። የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ባደረገው ምርመራም ከአዲስ ብድር እና ቁጠባ ተቋም መበደር ሳይሆን ሲቆጥብ የሚያሳይ ሰነዶችን ለማየት ችሏል።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፣ በኦዲት ሪፖርቱ ዘረፋ መፈጸሙ የተመላከተ ነገር ካለ በማለት ኦዲተሮችን ጠይቀው ነበር። ነገር ግን በዚህ መልኩ የጠፋ ንብረት አለመኖሩን ኦዲተሮች አረጋግጠዋል። ይሁን እንጂ ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስራ ላይ ሊከስር እንደሚችለው ማህበሩ ኪሳራ ሊያጋጥመው እንደሚችል አመላክተዋል።

**ከአዘጋጁ፤**

ከአራዳ ክፍለከተማ ወረዳ 09 እፎይታ የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የህበረት ስራ ማህበር ጋር በተያያዘ ቅሬታ ወይም ሀሳብ አለኝ የሚል አካል ከመጣ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆናችንን ዝግጅት ክፍሉ ይገልጻል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ባህልና በዓላት

### የሁለት ገጽ አንድነት፤

ወርሃ ነሐሴ በርከት ያሉ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላት የሚስተናገዱበት የደማቅ ክስተቶች ዕድለኛ ወር ነው። ዝናባማው የክረምቱ የአየር ጠባይ ስሜትን የማጨፍገግ ብርታቱ ጠንከር ያለ ቢሆንም አብዛኞቹ የወሩ ቀናት በባህላዊና በሃይማኖታዊ በዓላት የደመቁ ስለሆነ እንደ ተቀሩት የክረምት ወራት አውደ ዕለታቱ አኩርፈው ገብተው አኩርፈው የሚጠቡ አይደሉም። “ቡሄ ካለፈ የለም ክረምት” የሚለው ነባር አባባል የወሩን ቀናት ተስፈኝነት ይበልጥ አመልካች ነው። በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች ነሐሴ የሚጠራው የልጆችና የወጣቶች ደማቅ የበዓል ወር መባሉም ሌላው እውነታ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው። በነሐሴ ወር በቀዳሚነት የሚናፈቀውና የሚከወነው በጅራፍ ጩኸት የሚታጀበው የቡሄ በዓል የታዳጊ ልጆችና የወጣቶች ዋና ጉዳይ ስለሆነ ነው።

በሰሜናዊ የአገራችን ክፍል በድምቀትና ላቅ ባለ ፈንጠዝያ የሚከበሩት የሻደይ፣ የአሸንዳ/አሸንድዬ እና የሶለል ማራኪና ውብ የልጃገረዶች በዓላትም የዚሁ ወር የጸጋ ሰጦታዎች ናቸው። በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍ ባለ መንፈሳዊ ተመስጦ የሚከበረውና የወሩን እኩሌታ ያህል የሚሸፍነው ጾመ ፍልሰታም ሌላው የነሐሴ ወር በረከት ነው። ለጊዜው ያለንበትን ወር ነሐሴን በማሳያነት ጠቀስን እንጂ በእያንዳንዱ ወር የሚከበሩትን ማሕበራዊ፣ ሃይማኖታዊና መንግሥታዊ በዓላትን እየዘረዘርን ብንተርክ ብዙ ሊያጽፈን ይችላል።

የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ አሉን የምንላቸውን የባህሎቻችንን ዓይነትና ብዛት፤ የየበዓላቱን የአከባበር ሥርዓትና ወግ ወይንም የታሪካዊ ዳራቸውንና የትፈታቸውን የት መጣ በመዘርዘር ለመተንተን ታስቦ ሳይሆን ባህሎቹና በዓላቱ ለማኅበራዊ አኗኗራችን ምን ፋይዳ እንዳላቸው ለማመልከትና ድባቡ የሚፈጥረውን በጎ የስሜት ተጽእኖ በወፍ በረር ቅኝት ለማስታወስ ነው። ከዚያ በፊት ግን ስለ ሁለቱ ባህልና በዓል ጽንሰ ሃሳቦች ጥቂት መንደርደሪያ ሃሳቦችን እንፈነጣጥቅ።

አገራችን እጅግ በርካታና ውብ መንፈሳዊና ቁሳዊ የባህል ሀብቶች የታደለች እናም “የተመረቀች” ምድር ነች። በቋንቋ የበለፀገች፣ በመልክአ ምድር ውበትና የከርሰ ምድር ሃብቶቿ የምታማልል፣ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው የገዘፉ የታሪክ ቅርሶች ባለቤት፤ እኛነት በእኔነት፣ እኔነት በእኛነት ውስጥ ተዋህደው ዓለም በምሳሌነቷ የሚያደንቃት መሆኑም አይካድም፤ አይታበልምም።

ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፣ ኢ-አማኒው ከአማኒው ጋር ተጎራብቶ ብቻ ሳይሆን፤ ባህሉና በዓላቱ ሳይገድቡት ተጋብቶም ሆነ ተዋልዶ፤ ወይንም ተቀላቅሎ የሚኖርባት መሆኗም እሙን ነው። ታሪክ፣ ሃይማኖታዊ መጻሕፍትና የእምነቱ ሊቃውንት አዘውትረው እንደሚተርኩልን በቀድሞ ስማቸው ከሚታወቁት ከቂሳርያ፣ ከቁስጥንጥንያ፣ ከታናሹ እስያ፣ ከኪልቂያ፣ ከቆስያና ከአንጾኪያ ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ታሪካዊ ገዳማት የገደሙት ተሰዓቱ ቅዱሳን (“ዘጠኙ መነኮሳት” በመባል የሚታወቁት) የተስተናገዱት የአንድ ባህርይ (ተዋህዶ) ባህላቸውንና በዓላቶቻቸው ተከብሮላቸው ነበር።

ነብዩ መሐመድም “አላህ መፍትሔ እስኪያመጣ ድረስ ወደ ሐበሻ ምድር ብትሄዱ መልካም ነው። በእርሷ ማንም የማይበደልባት ንጉሥ አለ። የእውነት አገር ናት።” በማለት እዝነት በተሞላበት ስሜት አሥር ወንዶችንና አራት (አምስት የሚሉም አሉ) ሴት ስደተኛ ሙስሊሞች እንዲጠለሉባትና መሸሻ እንድትሆን የመረጡት ኢትዮጵያን ነበር። “አል ሃምዱሊላሂ ታቦታችን ገባ” እያለ ወሎዬው ሙስሊም በየጥምቀተ ባህሩ ታቦት እየሸኘ የሚዘምረው፣ በመንዙማ ዜማው እየዘየረ የክርስቲያን ወገኑን ሃይማኖታዊ በዓላት የሚያደንቀውና የሚከባበረው ሌላው ሃይማኖት ያልከለለው ድንቅ ውበታችን ነው።

ቤተክርስቲያን ሲታነጽም የአካባቢው ሙስሊም ወገን ለእርዳታና ለትብብር አለሁ የሚለውን ያህል፤ መስጊድ ሲገነባም ክርስቲያኑ ወገን ለሙስሊም ወገኖቹ ድጋፉን በፍቅር ጭምር እየገለፀ “ወገኔ ሆይ እኔም ለአንተ ጉዳይ ፈጥኖ ደራሽ ነኝ” እየተባባለ እርስ በርስ የሚደጋገፍ ሕዝብ ነው።

ሙስሊም ወገኖቻችን በሚያከብሯቸው የመውሊድና የአረፋ በዓላት ላይ የገና፣ የጥምቀትና የትንሣኤ በዓላትን የሚያከብሩ ክርስቲያኖች የሚታደሙት ማሕበራዊ ቁርኝታችን እንዳይላላ ተደርጎ ስለተጣመረ ነው። በክርስቲያኖቹ በዓላት ላይም እንዲሁ ሙስሊም ወገኖቻችን “እንኳን አደረሳችሁ” በማለት ደስታቸውን የሚገልጹት የኢትዮጵያዊነት እሴቱ ስላስተሳሰረን ነው። ይህን መሠል መከባበርና መቀባበል እንደ ሸማ የተከናነበ የብዝኋን ሃይማኖት፣ ባህሎችና በዓላት ባለፀጋ አገርና ወገን ይፈለግ ከተባለ አለጥርጥር ቀድማ የምትጠራው የእኛዋ አገርና ሕዝብ ነው።

እንደ ሀረሬ ቆነጃጅት አልባሳትና ጌጣጌጦች ቀለመ ደማቅና ማራኪ የባህል ውበትና ክብረ በዓላት ያላት ወይንም እንደ ባህላዊ “የአገር ባህል የጥበብ ልብስና ሸማችን” እርስ በእርሳቸው የተንሰላሰሉ የባህል ሀብቶችና በዓላት ያላት ይህቺ አገራችን ራሷ ጥበብ ናት ብለን ብንጠቀልል ሳይሻል አይቀርም።

### ባህል ምንድን ነው?

“ባህል” የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በምልዓት ለማብራራት መሞከር እንኳን ከሙያው ለራቁት ለተርታው የማሕበረሰቡ አባላት ቀርቶ ለእውቀቱ ቤትኞችም ሳይቀር ምልዑ የሆነ ድንጋጌ ለመስጠት እጅግ አዳጋች እንደሚሆን በዘርፉ ጠበብት ታምኖበታል። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ባህልን ለመደንገግ ሥነ-ሰብን (Anthropology)፣ የማኅበረሰብ ሳይንስን (Sociology)፣ ታሪክን (History)፣ ሥነ-መለኮትን (Theology) ፎክሎርን (Falklore) ወዘተ. በመሳሰሉ የጥናት ዘርፎች ላይ መብሰልን ግድ ይሏል። እንደዚያም ቢሆን እንኳን አጥኚዎቹ በምርምር መስካቸው ዙሪያ ይህንኑ የባህልን ጉዳይ አስመልክተው የሚሰጧቸው ብያኔዎች፣ ትንተናዎችና መከራከሪያዎች እጅግ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ እስካሁን አልጠለሉም።

የባህል ድንጋጌው ብቻም ሳይሆን፤ “የሰው ልጅ ከባህሉ ጋር ያለው ቁርኝት እስከ ምን ድረስ የጠነከረ ነው?” በሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ዙሪያም ቢሆን እስከ ዛሬ ድረስ በጋራ መግባባት ላይ አልተደረሰም። ምክንያቱም መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቡ ከራሱ ከባለቤቱ የሰው ልጅ ረቂቅ ተፈጥሯዊ ሰብእና ጋር እጅግ ስለተወሳሰበ ውሉን በቀላሉ ለማግኘት ያዳግታል። በየትኛውም ደረጃና የሕይወት አቋም ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ራሱን ከባህሉ ነጥሎ ለማውጣት በፍጹም አይችልም። አንዳንዶች እንደሚገልጹት ባህል ከራሱ ከሰው ልጅ የነርቭ ንዝረት ጋር በፅኑ የተቆራኘ ነው። ሌላው ቀርቶ ለሕይወትና ለፍልስፍና እምነቱ ሳይቀር የንጽረተ ዓለሙ መነጽር የተቃኘው በባህሉ ዙሪያ ነው።

ስለዚህም፤ ማንም ሰብአዊ ፍጡር ለባህሉ ተገዥ የሚሆነው ወዶ ሳይሆን የባህሉ ብርታት የግድ ብሎ ስለሚያስገብረው ነው። አንድ ምሁር እንደገለጹት “በፈጣሪ አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ በሥጋና በነፍስ የተሸረበ ሰብአዊ ፍጡር ነው። ከዚሁ እውነታ ባልተናነሰም ያለ ባህሉ ውበትና ድምቀት ሰብአዊ ማንነቱ ትርጉመ ቢስ ነው። “የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት ልዩ ፍጥረት ያሰኘው የሥጋና የመንፈሱ ህልውና ጣጣ ብቻ ሳይሆን የባህሉ ብርታት ጭምር ነው” የሚባለውም ስለዚሁ ነው። ስለ ባህል ጽንሰ ሃሳብ ከዚህ በላይ ሰፋ አድርጎ መተንተኑ ከመነሻ ዓላማችን ስለሚያዛንፈን እዚሁ ላይ መግታቱ ይመረጣል።

### በዓላትስ እንዴት ይደነገጋሉ?

አብዛኛውን ጊዜ በዓላት የሚቀዱት ከባህል ውቅያኖስ ውስጥ ነው። ከተለምዶ ሕይወታችን ተውስን ባህሎችንና በዓላትን በቀላልና ለንረዳው በምንችለው ተመሳስሎ እናነጻጽራቸው ከተባለም በተዋበ ኩታ ልንመስላቸው እንችላለን። በድርና በማግ የተሸመነው ዋነኛው መደረቢያ በባህል ቢመሰል፤ ኩታው የተዋበበትን ቀጭንና ዓይነ ግቡ ጥበብ ደግሞ ለበዓል ውክልና ልናውለው እንችላለን። ስለዚህም ነው የባህል የጥናት ዘርፍ ጎምቱዎች በዓላትን ከባህል ውበት መገለጫዎች መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው ብለው የሚበይኑት። በዓላት በአንጻባራቂ የባህል ፈርጥነትም ሊመሰሉ ይችላሉ።

### የበዓላት ማሕበራዊ ፋይዳ፤

ባህልም ሆነ በዓላት መንፈሳዊና ማሕበራዊ መስተጋብርን ለማሳለጥ ብቻም ሳይሆን ለግለ-ሕይወት ሁለንተናዊ ጤንነትም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ጉዳዩን ከራሳችን ዐውዳዊ የአኗኗር ይትባሃል ጋር በማስተሳሰር ሰፋ አድርገን እንፈትሸው። አብዛኛው የአገራችን ዜጋ አእምሮው በበርካታ ወቅታዊና ዘርፈ ብዙ ውጥረቶች የፊጥኝ ታስሮ እንዳለ ምስክር አያሻውም። ኑሮውና ኢኮኖሚው በቀሊል ሸክም ሳይሆን የቋጥኝ ያህል ተጭኖብን እያንገዳገደን እንዳለ ለማስታወስ ካልሆነ በስተቀር ለክርክር የሚጋብዝ አይደለም።

የውስጥና የውጭ ነባራዊ ሁኔታዎችና ችግሮች ከእንቅልፍም ሆነ ከእፎይታ አርቀውን ቆዛሚ አድርገውናል። የብዙዎች ሕይወት ተመሰቃቅሏል። በጦርነት የተፈናቀሉብን በሺህ ምንተ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ሲሆኑ ድርቅና ችግር ለስደት የዳረጋቸውም የዚያኑ ያህል በሚሊዮን ቁጥር የሚገለጹ ናቸው። የውስጥ ፖለቲከኞቻችንና የማሕበራዊ ሚዲያ ሰልፈኞችም ችግሮቻችንን እያጦዙ ተስፋችን እንዲመናምንና ብሶተኛ እንድንሆን ጫና እየፈጠሩ ፋታ ነስተውናል። አገልግሎት ለማስፈጸም ወደ መንግሥታዊ ተቋማት ጎራ ሲባል ያለው ውጣ ውረድና የሙሰኞች ዓይን ያወጣ ድፍረት “ወይ አገር!” እያሰኘ ያስቆዝመናል፤ ሲበረታም የእምባ ግብር ያስከፍለናል።

በዚህ ሁሉ ቱማታ መካከል ሕዝባችን ተረጋግቶ፣ ከውጥንቅጥ ኑሮውና ግራ ከተጋባበት ሕይወቱ ፋታ በማግኘት ለጥቂት ቀናትም ቢሆን በእፎይታ የሚተነፍሰው በበዓላት ሰሞን ነው። የኑሮ ጉዳተኛም ይሁን ኑሮው የተሳካለት ዜጋ የበዓል ሰሞን የሚኖራቸው ተስፋና መረጋጋት እጅግም ልዩነቱ የሰፋ እስከማይመስል ድረስ ሽር ጉዱ፣ በየቤተ እምነቱ እየተገኙ የሃይማኖታዊ ሥርዓቶችንና የአምልኮተ ፈጣሪ ልምምዳቸውን የሚፈጽሙት በተስፋ ስሜት ውስጥ ሆነውና በፈጣሪያቸው ኤልሻዳይነት እየተጽናኑ ነው።

ማጀቱ የተሚጠጠባቸውም ሆነ ማዕዳቸው የተትረፈረፈላቸው ዜጎች በእኩል ተመሳሳይ ስሜትና በጠንካራ እምነት በዓላትን ማክበራቸው ምናልባትም ልዩ መገለጫችን ይሆን ብለን ብንጠይቅ በራስ ውበት አፍቃሬነት ሊተረጎምብን አይገባም። በማጠናከሪያ የምናቀርበው ማስረጃ ሳይቀር እንኳን እኛ ባለጉዳዮቹ ቀርተን ባእዳን እንግዶችና ቱሪስቶች ሳይቀሩ በበዓላቶቻችን እጅግ እንደሚመሰጡ ምስክርነታቸውን ደጋግመን አድምጠናል። ይሄም ቢሆን ግን “በዓሉን በምን ጥሪቴ አድምቄ እንደ ሰው ተደስቼ ልዋል?” የሚሉ በጭንቀት የታፈኑ ድምጾች በፍጹም አይኖሩም ብሎ ለመከራከር አይቃጣንም። በሚገባ ይኖራሉና።

ይህንን መሰሉን ውስንነታችንን የሚቀርፍልን ትልቁ እሴታችን በበዓላት ሰሞንና ቀናት እየተጠራራን ቤት ያፈራውን መቋደሳችን ሁነኛ ማሳያ ነው። ስለዚህም በዓላት ለእኛ ማኅበረሰብ የዓውዳመት ፌሽታ መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ ለተወሰኑ ቀናት ያህል ከስሜት ህመም የሚፈውሱንና ተስፋችንን የሚያለመልሙ መድኃኒቶች ጭምር መሆናቸውን አስረግጠን እናሰምርበታለን።

እስካሁን አድምቀን ለማሞካሸት የሞከርነው የበዓላትን ስሜት ፈዋሽነትና ተስፋ አለምላሚነት ነው። ይህ ማለት ግን “በዓልን አራክሶ የከበረ፤ ጦም ገድፎ ያተረፈ የለም” በሚለው ብሂል ሥር ተጠልለን ሃይማኖታዊዎቹም ሆኑ ማሕበራዊ በዓላቶቻችን ከሥራ ሊያዘናጉን፣ ከእርሻ ሊያስተጓጉሉንና ከጥረታችን ሊያሳንፉን አይገባም። በሳምንት ሰባት ቀናት፣ በቀን ሃያ አራት ሰዓታት፣ ከወር ወርና ከዓመት ዓመት በዓላትን ካላከበርን ብለን እስረኛ እንዳንሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። ሁሉን በአግባቡ መያዙና ማስተናገዱ ተገቢ ስለሆነ። ሃሳባችንን የምንቋጨው በሚከተለው ማሳረጊያ ነው። ባህሎቻችንና በዓላቶቻችን ለስሜት ፈውስ፣ ለመረጋጋት እድል የሚፈጥሩልን ማረፊያዎቻችን መሆናቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ እነርሱን እያሳበብን በብክነትና በክስረት ውስጥ እንዳንወድቅና የበዓላቶቻችን ተጠቂዎች በመሆን የከፋ ችግር ላይ እንዳንወድቅ ኑሯችንን በጥበብና በማስተዋል ልንመራ ይገባል። ሰላም ይሁን!

# በቅዳሜ ገበያም የተጠናከረው የእሁድ ገበያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአገሪቱ እየተባባሰ ለመጣው የኑሮ ውድነት ከሚጠቀሱ በርካታ ምክንያቶች መካከል የምርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም አንዱ መሆኑ ይገለጻል፡፡ የግብይት ሰንሰለት መብዛትና አገራዊና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ለዋጋ ንረትና ለኑሮ ውድነት መከሰት ዓይነተኛ ድርሻ እንዳላቸውም ይታወቃል፡፡

በአገሪቱ እየታየ ያለውን የሸቀጦችና የግብርና ምርቶች የዋጋ ውድነትና ከዜጎች የመግዛት አቅም በላይ መሆንን የተረዳው መንግስት የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት መፍትሔ ያላቸውን የተለያዩ አማራጮችን እየወሰደ ይገኛል፡፡

መንግሥት ገበያውን ለማረጋጋት ከወሰዳቸው አማራጮች መካከል የህብረት ሥራ ማህበራትን በመጠቀም የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለሸማቾች ማቅረብ የሚለው ይገኝበታል፡፡ ምርቶቹን ደላላ ባልገባበት ሁኔታ የግብይት ሰንሰለቶችን በማሳጠር በህብረት ስራ ማህበራት መደብሮች በኩል በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራም ነው፡፡ በዚህም በኩል እንደ ስኳር፣ ዘይት፣ እህልና የመሳሰሉትን ለሸማቾች ቅርብ በሆኑ መደብሮች በኩል እያቀረበ ይገኛል፡፡

መንግስት ህብረተሰቡን ከኑሮ ውድነት የመታደጉን ስራ በማስፋት በአዲስ አበባ ከተማ የእሁድ ገበያዎችን ወደ ስራ በማስገባት ሸማቾች ምርቶችን በየአቅራቢያቸው በተቋቋሙ የእሁድ ገበያዎች አማካይነት ከአምራቾች ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በእነዚህ ገበያዎችም አትክልትና ፍራፍሬ፣ እህልና ሌሎች ምርቶች እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አማካኝነት የተጀመረው የእሁድ ገበያ የዋጋ ንረትን ለማርገብ ብሎም ገበያን ለማረጋጋት ጉልህ ድርሻ እየተጫወተ ይገኛል፡፡ የእሁድ ገበያ ሲጀመር ከፍተኛ ቁጥር ያለው የማህበረሰብ ክፍል በሚኖርበት አካባቢ ከአስር በማይበልጡ ቦታዎች ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ግን የክልል ከተሞችን ሳይጨምር በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 96 በሚደርሱ አካባቢዎች ቅዳሜን ጨምሮ በቋሚነት ግብይቱ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በእነዚህ የገበያ ቦታዎችም ሰፊ ቁጥር ያለው ሸማች በየሳምንቱ እየተገበያየ ነው፡፡ በተለይም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማህበረሰብ በሚንቀሳቀስባቸው እንደ መገናኛ፣ ሜክሲኮ፣ ጀሞና፣ ፒያሳ ጊዮርጊስና የመሳሰሉት አካባቢዎች ገበያው ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ሜክሲኮ ከሚገኘው የእሁድ ገበያ አትክልትና ፍራፍሬ ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ አበራ ማሞ በእሁድ ገበያው ደስተኛ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ ቅዳሜ ገበያ መጨመሩ የተሻለ እንደሆነና በየአካባቢው መገኘቱም ጠቃሚ ነው ይላሉ፡፡

ገበያው በየአካባቢው መኖሩ ሰዎች ከአካባቢያቸው ውጭ ሲንቀሳቀሱ እግረ መንገዳቸውን እንደየአቅማቸው መሸመት እንዲችሉ ያደርጋል የሚሉት አቶ አበራ፤ እርሳቸውም የእሁድ ገበያ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በየጊዜው የተለያዩ ምርቶችን ከገበያው ይሸምታሉ፡፡ በተለይ አትክልትና ፍራፍሬ በተመጣጣኝ ዋጋ እንደ ልብ የሚገኝ መሆኑን ነው ያስታወቁት፡፡ በሜክሲኮ፣ መገናኛና በሌሎች ዋና ዋና አደባባዮች አካባቢ ተወስኖ የነበረው የእሁድ ገበያ በአሁኑ ወቅት በየሰፈሩ እየታየ መሆኑንም የገበያ ተደራሽነት እየሰፋ እንዲመጣ እንዳደረገ ይናገራሉ፡፡

ከእሁድ በተጨማሪ ገበያው ቅዳሜም መኖሩ ደግሞ እሁድ የማያመቸው ቅዳሜ እንዲሸምት ማስቻሉንና ሌላው ጥሩ አማራጭ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በዚሁ ገበያ የተለያዩ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚገኙ የሚናገሩት አቶ አበራ፤ በዋጋ በኩልም ከሱቅ ከሚገዙበት ዋጋ መጠነኛ ቅናሽ እንዳለው ነው ያስታወቁት፡፡ የገበያው ቦታ ሜዳ ላይ መሆኑ ግን ለሸማቹም ሆነ ለአቅራቢዎቹ ምቹ አይደለም ሲሉ እንደ ችግር ያነሳሉ፡፡

እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በሚል የተጀመረው የእሁድ ገበያ አሁን ላይ ቅዳሜን ጨምሮ በየአካባቢው እየሰፋ መጥቷል፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ዘንድ ተደራሽ መሆን የቻለው የእሁድ ገበያ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ያለው ሂደት ምን ይመስላል? የታለመለት ዓላማንስ አሳክቷል ወይ? ያጋጠሙ ችግሮችስ እንደምን ያሉ ናቸው? ስንል ላነሳነው ጥያቄ በአዲስ አበባ ከተማ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የግብይትና የገበያ መሰረተ ልማት ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ ደብሪቱ ለዓለም ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የእሁድ ገበያ ከተጀመረ ከ42 ሳምንታት በላይ እንደሆነው ወይዘሮ ደብሪቱ ያስታውሳሉ፡፡ ገበያው አስር በማይሞሉ አካባቢዎች የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ምንም ሳይቆራረጥ በ96 ቦታዎች እየተካሄደ ነው ይላሉ፡፡ በዚህም ህብረተሰቡ ከገበያው ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ መቻሉን ይገልጻሉ፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ቅዳሜን ጨምሮ በ96 የተለያዩ አካባቢዎች በየሳምንቱ እየተካሄደ ያለው የእሁድ ገበያ ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ በርካታ ሰዎች ይገኙበታል፤ ማዕከል ናቸው ተብለው በሚገመትባቸው አካባቢዎች ብቻ ይደረግ ነበር፤ በዚሁ ገበያ የአካባቢው ማህበረሰብ ሳይሆን የሚጠቀመው መንገደኛው ብቻ ነው የሚል አስተያየት ኤጀንሲው የደረሰውን መሆኑን ተከትሎ ገበያውን ማስፋት ውስጥ ተገብቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት በየሳምንቱ እሁድ እንዲሁም ቅዳሜ በየአካባቢው በሚገኙ የሸማች ህብረት ሱቆች አካባቢ ድንኳን ተዘርግቶ ምርቶቹ ለማህበረሰቡ መቅረብ እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

በዚሁ ገበያ የሚቀርበው ምርት ተመጣጣኝ ዋጋ፤ ትኩስና ጥራት ያለው እንደሆነ የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ በተለይም አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የተለያዩ የግብርና ምርቶች መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረቡ ስለመሆናቸው ያብራራሉ፡፡ ለአብነትም ሶስት አይነት ጤፍ በጥሬውና ተፈጭቶ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰዋል፤ ሸማቾች ጤፍ እንደየአቅማቸው መሸመት እንዲችሉ ከአምስት ኪሎ ጀምሮ ታሽጎ እየቀረበ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ ለገበያ የሚቀርቡት ምርቶችም በተለያዩ ሸማች የህብረት ሥራ ማህበራት እየቀረቡ ሲሆን፣ በዚህ ስራ የተሰማሩት የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራትም በአሁኑ ወቅት 150 መድረሳቸውን ያብራራሉ፡፡

በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ አትክልትና ፍራፍሬ ይዘው የሚቀርቡት በተለይ አምራቾች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ አምራቾቹ የተለያዩ ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለሸማቾች የሚያቀርቡበት ሁኔታ መፈጠሩን ይናገራሉ፡፡ ምርቶቹም ትኩስና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መሆናቸውን ነው ያስረዱት፡፡ ከምርቶቹም መካከል ሽንኩርት፣ ድንች፣ ካሮት፣ ቲማቲም፣ ፎሶሊያ፣ ጎመንና ሌሎችም ይገኙበታል። ፍራፍሬዎችም እንዲሁ አቦካዶ፣ አናናስ፣ ሙዝ፣ አፕልና ሌሎችም ፍራፍሬዎች እንደየወቅቱ ሁኔታ በየሳምንቱ በገበያው ይቀርባሉ ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ዳይሬክተሯ እንደሚሉት፤ በየአካባቢው የሚገኘው የማህበረሰብ ክፍልም ምርቶቹን በአቅራቢያው ማግኘት በመቻሉ በደስታ በሰልፍ ጭምር ወረፋ ይዞ እየሸመተ ይገኛል፡፡ በተለይም በስፋት በገበያው የሚቀርቡትን አትክልትና ፍራፍሬዎች በየሳምንቱ እየሸመተ ስለመሆኑ ራሳቸውም ማረጋገጥ ችለዋል፡፡

ማህበረሰቡ ምርቶቹን የሚገበይበት ቦታ ራቅ ያለ እንደነበር አስታውሰው፣ በሁለት ሳምንትና በወር አንድ ጊዜ ብቻ ይሸምት እንደነበርም ይናገራሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ገበያው ለየአካባቢው እንዲቀርብ መደረጉን ተከትሎ የትራንስፖርት ወጪ ሳያወጣና ጊዜውን በሚቆጥብና አቅሙን ባገናዘበ መልኩ በየሳምንቱ እየሸመተ እንደሆነ መረዳት ችለናል ይላሉ፡፡

‹‹በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሁም ጥራት ያለውና ትኩስ ምርት በየሳምንቱ ስለማግኘቱ ማህበረሰቡ ግብረ መልስ እየሰጠ ነው›› ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የሚቀርቡ የግብርና ምርት አይነቶች እንደየጊዜው እንደሚለያዩም ነው የተናገሩት፡፡ ለአብነትም የእሁድ ገበያ በተጀመረበት አካባቢ የሚቀርቡ ምርቶች ጥራት ያላቸውና ተመጣጣኝ ዋጋ እንደነበራቸው ያስታውሳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የሽንኩርት ዋጋ በከፍተኛ መጠን መጨመሩን፣ ያለውም በጥራትና በመጠን ያነሰ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ይህም ወቅቱ ክረምት በመሆኑና መኪኖች እርሻ ውስጥ ገብተው ለመጫን ካለመቻላቸው ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ችግር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

‹‹ሽንኩርት የመበላሸትና የመበስበስ ባህሪ አለው፤ ለገበያ የሚቀርበው ሽንኩርት መጠንና ዋጋውም የሚጨምርበትና የሚቀንስበትም ወቅት አለው፡፡›› ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ህብረተሰቡ ጊዜውን በመረዳት መታገስ ይገባዋል›› ብለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የሽንኩርት እጥረትና በዋጋም መወደድ ምክንያታዊ መሆኑን ነው ያስረዱት፡፡ ሽንኩርት ላይም ሆነ ሌሎች ምርቶች ላይ ለአብነትም ሙዝ ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ግሽበት ከወቅትና ከምርት እጥረት ጋር ተያይዞ የመጣ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ዳይሬክተሯ እንዳስታወቁት፤ ወቅታዊ ከሆኑ ችግሮች ውጭ ያሉትን ችግሮች በመፍታት ገበያው ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በቅንጅት እየተሰራ ነው፡፡ ከወረዳ እስከ ማእከል ባሉ የንግድ ቢሮ አመራሮችና ባለሙያዎች፤ የህብረት ሥራ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም በከንቲባ ደረጃ የተቋቋመ ግብረ ኃይል ጭምር ገበያውን በመከታተልና በመቆጣጠር እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ለአብነትም የምርት እጥረት ባለበት አካባቢ ምርት እንዲቀርብ በማድረግ ማህበረሰቡ ከሚሰጠው አስተያየት በመነሳት ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከኢንዱስትሪ ምርቶች ጋር ተያይዞ የስንዴ ዱቄት አቅርቦት አለመኖሩን አስመልክቶ የጠየቅናቸው ዳይሬክተሯ በሰጡት ምላሽ፤ አቅርቦቱ የተስተጓጎለው የምርት እጥረት ከመኖሩ ጋር በተያያዘ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ በጥሬ ዕቃ እጥረት ምክንያት የፓስታና የመኮረኒ ምርት እጥረት ስለመኖሩም ነው የጠቆሙት፡፡

የስንዴ እጥረት በእነዚህ ምርቶች ላይ እያሳደረ ካለው ተጽዕኖ ውጭ በሌሎች ምርቶች በተለይም የግብርና ምርቶች የሆኑ አትክልትና ፍራፍሬ የመሳሰሉት ግን በተመጣጣኝ ዋጋ በጥራት ለማህበረሰቡ እየቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ብዛት እየጨመረ የመጣ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ አቅርቦቱን ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ማድረግ የማይቻል እንደሆነ ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ በተቻለ አቅም አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ 11 ክፍለ ከተሞችና በ19 ወረዳዎች በሚገኙ 150 ሸማች የህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የተለያዩ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ሳምንቱን በሙሉ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት ለህብረተሰቡ ደራሽ መሆናቸው ታምኖበት መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ድጎማ ማድረጉን ያስታወሱት ዳይሬክተሯ፤ በተለይም ከ2013 ዓ.ም እስከ 2014 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ድረስ የጤፍ ዋጋን ማረጋጋት መቻሉንና ይህም በመንግስት በኩል የተደረገው ትልቅ ድጋፍ ውጤት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ምርቱ ከአምራች ህብረት ሥራ ማህበራት በአስር ዩኒየኖች አማካኝነት እየመጣ በመሰረታዊ ሸማች ማህበራት በኩል ለማህበረሰቡ እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ መሰረታዊ ሸማቾችም ማህበረሰቡ እንደየአቅሙ መሸመት እንዲችል ጥሬ ጤፍ፣ የተፈጨ ጤፍና እንጀራ በመጋገር ጭምር ለማህበረሰቡ እንደየፍላጎቱ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም መንግሥት እያገዘ በመሆኑ ነው፡፡

ማህበረሰቡም ከሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት የሚያገኘውን ጥቅም በመረዳት በስፋት እየተጠቀመ እንደሚገኝ ተናግረው፣ ከፊቱ በተሻለ ጥራት ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የእሁድ ገበያ የተነሳበትን ዓላማ ማሳካት ችሏል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በተለይም የጤፍ ዋጋ እንዲረጋጋ ማድረግ መቻሉን ነው ያስታወቁት፡፡ ለአብነትም ነጭ ጤፍ በአሁኑ ወቅት በግለሰብ ነጋዴዎች ደረጃ በኪሎ 56 ብር መሆኑን ጠቅሰው፣ ዋጋ በሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት 48 ብር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ሰርገኛ ጤፍም በኪሎ 44 ብር ሲሸጥ በሌሎች የገበያ ቦታዎች ግን በኪሎ 52 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑን ነው የገለጹት፡፡ ይህ ሰፊ የዋጋ ልዩነት የታየበት ምክንያት መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

ይሁንና አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል በሳምንት ሁለት ጊዜ የተለያዩ ምርቶችን ማግኘት ባስቻለው የእሁድ ገበያ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶች እንዲሁም የእንስሳት ተዋጽኦን ጨምሮ በኪሎ ከአምስት ብር እስከ አስር ብር ቅናሽ እያገኘ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

መንግሥት የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ባደረገው ከፍተኛ ጥረት አሁን ድረስ በሸማች የህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ጤፍን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማህበረሰቡ ጤፉን እዛው ገዝቶ አስፈጭቶ መውሰድ እንደሚፈልግም ይገልጻሉ። አብዛኞቹ ወፍጮ ቤት የሌላቸው መሆኑን ማህበረሰቡ የሚያነሳው ቅሬታ እንደሆነም ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ ይህን ችግር ለመፍታትም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ ዩኒየኖች የመጋዘን እጥረት ያለባቸው በመሆኑ ሌላኛው ችግር ነው፡፡ የመጋዘን ችግሩንም ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የገበያ ቦታም ምቹ አለመሆንም ሌላው የሚነሳ ተግዳሮት ነው፡፡ በተለይም ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ቅዳሜና እሁድ ሠራተኛ ይዘው ድንኳን ተከራይተው የሚወጡ በመሆኑ አትራፊ አይደሉም፡፡ በትንሹ ለአንድ ድንኳን ከ500 እስከ 700 ብር ድረስ ያወጣሉ፡፡ ይህ አንድ ችግር ነው፡፡

በቀጣይም በእሁድ ገበያው ያጋጠሙ ችግሮችን በመፍታት ገበያውን በቋሚነት ለማስቀጠል ጥናት እየተካሄደ እንደሆነ ያመላከቱት ዳይሬክተሯ፤ እስካሁን ባለው የእሁድ ገበያም ከአራት መቶ ሚሊዮን ብር በላይ መገበያየት መቻሉን ተናግረዋል፡፡



የእሁድ ገበያዎች እንደ አትክልትና ፍራፍሬ ያሉ የግብርና ምርቶች በስፋት እየቀረቡባቸው የኑሮ ውድነትን ለመከላከል እያስቻሉ ናቸው፤

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የእግዜር ውሃ ስትገረው የታሸገ ውሃ ምኑ ነው?

**ደበል ካሳ**

ከሰሞኑ መነጋገሪያ ከነበሩ ጉዳዮች መካከል በጥንታዊቷና ከሁለት ምዕተ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ መዲና ሆና ባገለገለችው የጎንደር ከተማ የተፈጠረው ከፍተኛ የመጠጥ ውሃ እጥረት ችግር አንደኛው ነው፡፡ ለከተማው የንጹህ የመጠጥ ውሃ መጠን በቀን 70 ሺህ ሜትር ኪዩብ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት እየቀረበ ያለው 13 ሺ ሜትር ኪዩብ ብቻ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ካለፈው የሰኔ ወር ጀምሮ የከተማዋ ነዋሪዎች 90 በመቶ የሚሆነውን የውሃ ፍጆታቸውን የሚያገኙት ከዝናብ ውሃ መሆኑን ችግሩን አስመልክቶ ከሁለት ሳምንት በፊት በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በክልሉ መንግስትና በከተማው ነዋሪዎች መካከል በተደረገ የምክክር መድረክ ላይ ተገልጿል። በመሆኑም በከተማዋ የንፁህ መጠጥ ውሃ ማግኘት ፈታኝ እየሆነ ከመምጣቱ ባሻገር በከተማዋ የቱሪዝምና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር በመጀመሩና ችግሩ የከፋና አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ጉዳዩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ በበጀት የተደገፈ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥበትም ነዋሪዎቹ ጠይቀዋል፡፡

በመዲናችን አዲስ አበባም በተመሳሳይ እንደ ጎንደሩ የከፋ ባይሆንም ከፍተኛ የውሃ እጥረት ችግር መኖሩ ይታወቃል፡፡ ሳምንት ጠብቀው ውሃ የሚያገኙ የመዲናችን ነዋሪዎችና አካባቢዎች(ሰፈሮች) በርካታ ናቸው፡፡ የአፍሪካ የውሃ ማማ በምትባል አገር መጠኑ ይለያይ እንጂ ከአርብቶ አደር እስከ አርሶ አደር፣ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከቆላ እስከ ደጋ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እጥረት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ችግር መሆኑ ለሰሚው ግራ ነው ከማስባል አልፎ ቆም ብለን እንድናስብ የሚያስገድድ ነው፡፡

በሌላ በኩል ውሃ አሽገው የሚሸጡ የንግድ ድርጅቶች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው፣ እንደ አሸን እየፈላ ነው ቢባል ይቀላል፡፡ ይሁን እንጂ የታሸገ የንግድ ውሃ ዋጋም እንደሌሎች ሸቀጦች በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው፡፡ በእርግጥ እዚህ አገር ያልተወደደ ነገር የለም፡፡ ዳቦ አንድ ከብር ተነስቶ አስር ብር ደርሷል፣ እንጀራም እንደዚሁ... ሸንኩርት...ዘይት...ነዳጅ ...አሁን ደግሞ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ የሚገባ የሚመስል ውሃ፣ የእግዜር ውሃም እየተወደደብን ነው፡፡ እየተወደደ ብቻ ሳይሆን እያጠረ ነው፡፡ የተወደደውማ የንግዱ የታሸገ ውሃ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ነገር አንድ ታዋቂ የፀረ አዲስ ዓለም ሥርዓት አንቂ በአንድ ወቅት የጻፈውና በአንድ ወቅት ያነበብኩትን ፅሁፍ ደግሜ እንዳስታውሰው ያደርገኛል፡፡

ግማሽ ሊትር ውሃ አስራ ሁለት ብር፤ አንድ ሊትር አስራ ሰባት ብር፣ ሁለት ሊትር ውሃ ደግሞ ሃያ አምስት ብር ገብቷል፡፡ አስቡት እንግዲህ የአፍሪካ የውሃ ማማ በሆነችው የአፍሪካ መዲና ላይ አንድ ብርጭቆ ውሃ አስር ብር ሲሸጥ፤ ለዚያውም ሳንፈልግ በግዴታ፡፡ ምክንያቱም በብዙ የመዲናችን(የአገራችን ተመሳሳይ ነው) ሬስቶራንቶች ተመጋቢው የእግዜር ውሃ የማግኘት መብት የለውም፣ ምግቡ እንዳያንቀው መጠጣት የሚችለው የታሸገ ውሃ ገዝቶ ነው፡፡ ይታያችሁ እንግዲህ አስገድደው ሲሸጡልን፡፡ ታዲያ ይኼ በእርግጥም የብዙሃኑ መሆኑ ቀርቶ ውሃም እንደ ውስኪ የሃብታሞች ብቻ ወደ መሆን እየተሸጋገረ አይደለም ትላላችሁ? እውነቴን እኮ ነው፡፡ እስኪ እኔስ የመንግስት ሰራተኛ በመሆኔ ቢያንስ ድሃ በሚለው ምድብ ውስጥ ስለሆንኩ እንደምንም ብዬ ግማሽ ሊትር ውሃ በአስራ ሁለት ብር ገዝቼ ልጠጣ እችላለሁ፡፡ ቆይ ከእኔ ያነሰ ገቢ ያላቸውስ፤ ማለቴ ይች አገር እኮ ከድሃም ያነሰ "የድሃ ድሃ" የሚባሉ ዜጎች የሚበዙባት አገር ናት፡፡ ታዲያ ቢቀር ቢቀር ውሃም "ጥቁር ውሃ"ም ይወደድብን እንዴ?

እናም "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" እንዲል ያገሬ ሰው እዮሃኪም ሃጎፒያን የተባሉ የፀረ አዲሱ ዓለም አንቂ እንደሚሉት የእኛዎቹ ውሃ ሻጭ ቱጃሮችም የዓለም አቀፉ "ውሃን በሞኖፖል የመያዝ" ሴራ አካል እንዳልሆኑ በምን እርግጠኛ እንሆናለን፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት ውሃን በግል ይዞታ ስር የመቆጣጠርና የህዝብ ቁጥርን በፍጥነት የመቀነስና ዓለምን ለራሳቸው ብቻ በሚመች መልኩ አፍርሶ ለመስራት ከመጋረጃው በስተጀርባ እየተካሄደ ያለ ድብቅ አጀንዳ አለ፡፡ ሴራው የኃያላን አገራት መንግስታት ድጋፍ ያለው መሆኑንም ተሟጋቹ በመረጃ ይከራከራሉ፡፡ በዓለም ባንክ ስር የሚተዳደረው "ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን" በየዓመቱ በርካታ ሚሊዮን ዶላሮችን በብድርና በእርዳታ መልክ የሚሰጥ በተለይም በድሃ አገራት የውሃን የግል ይዞታነት ለማስፋፋት ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች በዓለም ላይ ትልቁ የገንዘብ ምንጫቸው መሆኑንም በማስረጃነት ይጠቅሳሉ፡፡ እናም ተራው የዓለም ህዝብ በአንድነት ሆ ብሎ ተነስቶ ካልተቃወመውና ካላስቆመው በስተቀር በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕቅዳቸው እንደሚሳካ ያስጠነቅቃሉ፡፡ በዚህ ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ላይ የውሃን የግል ይዞታነት የሚቃወሙ ድምጾች እየተበራከቱ መምጣታቸው የመጥፋት አደጋ ለተጋረጠበት ብዙሃኑ የዓለማችን ምስኪን ህዝብ መልካም ዜና ነው ይላሉ እዮሃኪም ሃጎፒያን፡፡ ዓላማቸውም ይኸው ነው የውሃ አቅርቦት በእነሱ ቁጥጥር ሥር ይውላል፣ ገንዘብ የሌለው ብዙሃኑ ድሃ የሚጠጣው ውሃ ስለማያገኝ በውሃ ጥም፣ የሚታጠብበትና ንጽህናውን የሚጠብቅበት ውሃ ስለማይኖረው በወረርሽኝ በሽታ እንዲያልቅ ማድረግ፤ ከዚያም እንደተመኙት "በሃብታሞች፣ ለሃብታሞችና የሃብታሞች ብቻ የሆነች አዲስ ዓለም መፍጠር(Realizing their dream of creating the New World Order)"!

ለዚህም ከሁለት ዓመት በፊት የዓለም ባንክ ዓመታዊ ጉባኤውን በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ባካሄደበት ወቅት ከህንድና ከአሜሪካ የተውጣጡ የውሃ የግል ይዞታን የሚቃወሙ ፀረ ኮርፖሬታውያን ዓለም አቀፍ ጥምረቶች "የዓለም ባንክ በታዳጊ አገራት ላይ በልማት ስም ውሃ በግል ይዞታ ሥር እንዲውል የሚያደርገውን ዘመቻ እንዲያቆም እንጠይቃለን" በማለት በግልጽ ደብዳቤ መጠየቃቸውና ለዓለም ህዝብ መልዕክት ማስተላለፋቸው አንዱ ማሳያ ነው፡፡

እናም ብዙሃኑ ድሃ ህዝብ ኮርፖሬታውያኑ ከቃጡበት ጥፋት ራሱን በፍጥነት መታደግ ከፈለገ ከላይ እንደተጠቀሱት የህንድና የአሜሪካ የጋራ ጥምረት አባላት በንቃት ሊታገል ይገባል፡፡ ሰፊው ህዝብ እንዲህ በአንድነት ሆ ብሎ ከተነሳና ከተባበረ ደግሞ ለሰው ልጆች ሕይወትና ደህንነት ሁሌም ከኮርፖሬታውያኑ ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀው እኩይ ሴራቸውን በድፍረት እያጋለጡና በፅናት እየታገሉ የሚገኙት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት አርበኞችና የመብትና የደህንነት ተሟጋቾች ከጎኑ ናቸው፡፡ እናም የቀድሞው የጦር መኮንን ሚስተር ኢዮሃኪም ሃጎፒያን ግሎባል ሪሰርች ላይ በጻፉት ጽሁፋቸው "ምስኪኑ ድሃ ወገኔ ሆይ ራስህን ለማዳን ጊዜው አሁን ነው፡፡ በተባበረ ክንድህ ፈጥነህ የጥፋት ሴራ አክሽፍ!" የሚል የሕይወት አድን ጥሪ ለዓለም ህዝብ ያስተላልፋሉ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፍትሕ መሥሪያ ቤትን ከሰሱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ ጠበቆች የአሜሪካ ፍትሕ መሥሪያ ቤት ላይ ክስ መሠረቱ።

ክሱን የመሠረቱት የፌደራል የወንጀል ምርመራ ቢሮ (ኤፍቢአይ) አላግባብ በዶናልድ ትራምፕ ቤት ላይ ፍተሻ አድርጎ ሰነዶችን በጉልበት ወስዷል በሚል ነው፡፡

ፍሎሪዳ የሚገኘው የትራምፕ ቅንጡው ማራ ላጎ መኖሪያ ቤት በፖሊስ ድንገተኛ ወረራ እና ብርበራ የተደረገበት በቅርቡ ነበር፡፡

ብርበራውን ተከትሎ በአሜሪካ ከፍተኛ የፖለቲካ ክርክር ትኩሳት ተቀስቅሷል፡፡ በዲሞክራቶችና በሪፐብሊካኖች መካከልም ለተጋጋለ ፖለቲካዊ ሙግት በር ከፍቷል፡፡

ይህን የፖሊስ ብርበራ ተከትሎ የአሜሪካ ፍትሕ መሥሪያ ቤት ከፍተኛ የአገር ምሥጢር የነበሩና ትራምፕ መኖሪያ ቤት መቀመጥ ያልነበረባቸው የተባሉ ጥብቅ ሰነዶችን ማግኘቱን ይፋ አድርጓል፡፡

ወትሮ በእንዲህ ያለ ጊዜ የምርመራ ቢሮ ከፍርድ ቤት የብርበራ ፈቃድ ካገኘ በኋላ በብርበራ ስለተገኙ ሰነዶች ምንነት ምርመራ ሳይጠናቀቅ ይፋ አያደርግም፡፡

ሆኖምበፍትሕ መሥሪያ ቤቱ ላይ የደረሰውን ሕዝባዊ ትችት ለማርገብ የዚህ መሥሪያ ቤት አለቃ በብርበራው የተገኙ ሰነዶችን ይዘት በደምሳሳው ምን እንደሆኑ ፍንጭ ለመስጠት ተገደው ነበር፡፡

ከትራምፕ ጠበቆች አንዱ ደግሞ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሦስተኛ ገለልተኛ አካል ተመድቦ ነገሩን ያጣራ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የፍትሕ ቢሮ ለዚህ ክስ በሰጠው አጭር ምላሽ



አቃቢ ሕግ በትራምፕ ላይ እየተደረገ ያለውን ምርመራ እንዲያውቅና በፍርድ ቤት ተገቢውን ምላሽ እንደሚሰጥ ተጠቁሟል፡፡

የፍትሕ ቢሮ ቃል አቀባይ አንተኒ ኮሊ እንዳሉት የማሮላጎ ብርበራን በተመለከተ ፍርድ ቤት የብርበራ ፈቃድ ካተመ በኋላ የተደረገ ሕጋዊ መስመርን የተከተለ ነው ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

የትራምፕ ጠበቆች ለፍሎሪዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የ27 ገጽ ክስ፣ የአሜሪካ ምርመራ ቢሮ ትራምፕ ወደፊት ለአሜሪካ ፕሬዝዳንትነት በድጋሚ እንዳይወዳደሩ ለማድረግ የሸረበው ሴራ ስለሆነ ሰነዶቹን አሁኑኑ ይመልስ፣ ምርመራውን ዛሬ ነገ ሳይል ያቁምልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

## ቻይና ከሩሲያ የምታስገባው የኃይል አቅርቦት መጠን ጭማሪ አሳየ



ቤጂንግ እንደ መረጃው ከሆነ ከመጋቢት እስከ ሐምሌ ባለው ጊዜ ከሩሲያ የምትገዛው የነዳጅ ድፍድፍ፣ የነዳጅ ዘይት፣ የጋዝ እና የድንጋይ ከሰል ምርቶች ግዢ ከዓመት በፊት ከነበረው 20 ቢሊየን ዶላር ወደ 35 ቢሊየን ዶላር አድጓል።

የሩሲያ ዩክሬን ግጭት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ምዕራባውያን በሞስኮ ላይ ከጣሉት ማዕቀብ በኋላ ከሩሲያ ወደ ቻይና የሚገቡ የኃይል አቅርቦት ምርቶች ከ75 በመቶ በላይ መጨመራቸውን የቻይናን የቅርብ ጊዜ የጉምሩክ አሃዞች በመጥቀስ ብሉምበርግ ዘግቧል።

ለግዢው መጨመርም ከምዕራባውያን ማዕቀብ በኋላ ሩሲያ በሃይል አቅርቦት ምርቶቿ ላይ ያደረገችውን ቅናሽ ቻይና እንደመልካም አጋጣሚ መጠቀሟ ነው ተብሏል፡፡

ቻይና በሐምሌ ወር ብቻ ከሩሲያ 7 ነጥብ 4 ሚሊየን ቶን የድንጋይ ከሰል በማስገባት ከፍተኛውን ግዢ ስትፈጽም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ14 በመቶ ብልጫ አለው ነው የተባለው።

በሐምሌ ወር ከሩሲያ ወደ ቻይና የሚገባው የነዳጅ ድፍድፍ ከሰኔ ወር በትንሹ የቀነሰ ቢሆንም ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር አሁንም በ8 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑ ተገልጿል።

ቻይና ከሩሲያ የተገበያየችው የተፈጥሮ ጋዝም ካለፈው ዓመት የ20 በመቶ ብልጫ ማሳየቱ ተጠቅሷል፡፡

ይህ አሃዝ ከሩሲያ ወደ ቻይና በዋናው የትራንስፖርት መስመር ቧንቧ የሚገባውን ነዳጅ እንደማያካትት ዘገባው አስታውሷል፡፡

በአጠቃላይ ቻይና በሐምሌ ወር ከሩሲያ ላስገባችው ነዳጅ 7 ነጥብ 2 ቢሊየን ዶላር ወጪ እንዳደረገች የተገለጸ ሲሆን ባለፈው አመት በዚሁ ተመሳሳይ ወር ያወጣችው ወጪ 4 ነጥብ 7 ቢሊየን ዶላር እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# መራሄ-ተውኔት አባተ መኩሪያ
## (1932 -2008 ዓ.ም)

ግርማ መንግሥቴ

የዛሬው ንባባችን ወደ ኪነጥበቡ፣ በተለይም ወደ ትያትሩ አለም ያዘነበለ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዛሬ የምናስታውሰው ባለውለታችን ሙያዊ ማንነት በርእሳችን እንደገለፅነው መሆኑና በዚሁ ዘርፍ አንቱ የተባለ ባለሙያ መሆኑ ነው።

እንደማንኛውም ዘርፍ በኪነጥበቡ አለም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ አንጋፎች ያሉ ሲሆን አንዱም ትያትርን ሕይወቱ አድርጎ ያለፈ፣ ራሱን ለሙያው አሳልፎ የሰጠ፤ ለ50 ዓመታት ለኢትዮጵያ ትያትር የጀርባ አጥንት ሆኖ የቆየ፣ በኢትዮጵያ ኪነጥበብ ታሪክ ውስጥ አሻራውን ያሳረፈ፤ በሙዚቃዊ ትያትር ዘርፍ ፈር ቀዳጅ ስራዎችን ወደ መድረክ ያመጣ፣ ታሪካዊ ትያትሮችን የሚገባቸውን ደረጃ ሰጥቶ የሚሰራ ( “ቴዎድሮስ”፣ ከስድስት ዓመት በሁዋላ ለመድረክ ያበቃው “አሉላ አባ ነጋ” እና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የተሳተፉበት፣ የ”አድዋ”ን የክተት ዘመቻ የሚያሳይ እና በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ ያቀረበው ትርኢት ይጠቀሱለታል) የተባለለት፣ በአባቱ ስም "መኩሪያ ቲያትር" መጽሔት ለህትመት የበቃለት፤ ሙያውን ሰርቶ ሳይጠግብ እድል በመነፈጉ “መድረክ እንዳላገኝ ተደርጌያለሁ” በማለት ብሶቱን ሲያሰማ የነበረው፤ ከማንም ጋር መግባባት የሚችለው ... መራሄ-ተውኔት አባተ መኩሪያ ነው።

በብዙዎቻችን ”ጋሽ አባተ” በሚል ማህበራዊ ማእረግ የሚጠራው አባተ መኩሪያ ትያትር ሙያው የነበረ ሲሆን፤ ከባለ ሙያነት ባለፈም ለዘርፉ ልማት ከፍተኛ መስዋእትነትን የከፈለ፤ በዘርፉ በርካታ ስመ ጥር ባለ ሙያዎችን ያፈራና በሙያው አገሩን ለአለም ያስተዋወቀ፤ ሲበዛ ብርቱና በሚዲያው ዘርፍም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተ አንጋፋ ባለውለታ ነው። (በጋሽ አባተ አማካኝነት 5ኛው የምስራቅ አፍሪካ የኪነጥበባት ፌስቲቫል እዚህ ኢትዮጵያ ሲካሄድ ይህ ጸሐፊ ከእሱ ጋር ለወራት (ካሳንችስ በነበረው ቢሮው) አብሮ የመስራት እድል ገጥሞት የነበረ በመሆኑ እነዚህን የጋሽ አባተን መለያዎች በቅርብ ተመልክቷል።)

ጥበብ የባተው አዘጋጅ፣ የውዝዋዜ አሠልጣኝ (ኬሪዮግራፈር)፣ ጸሐፌ ተውኔት፣ የፊልም አዘጋጅ የነበረው አባተ መኩሪያ በአገሪቱ የቴአትር ታሪክ ውስጥ ስማቸው በግዙፍ ከሚነሱትና አሻራቸውን ካሳረፉት መካከል አንዱ ነበር። በተለይ በተውኔት አዘጋጅነት ስመ ጥር ለመሆኑ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎቹ ይመሰክራሉ።

በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አገራት (ጀርመን፣ እንግሊዝ፣ አየርላንድ፣ አሜሪካ ...) የትያትርና ሌሎች የጥበብ ስራዎች አዘገጃጀትን የቀሰመው፤ በተለያዩ አገራትም ትምህርታዊ ጉዞዎችን ያደረገው ጋሽ አባተ፤ ከሥራዎቹ መካከል ሀሁ በስድስት ወር (1966) አቡጊዳ ቀይሶ (1971)፣ መልእክተ ወዛደር (1971)፣ የመንታ እናት (1971)፣ መቅድም (1972)፣ ጋሞ (1973)፣ አሉላ አባነጋ (1979) ይጠቀሳሉ። (ብዙዎቹ አባተ ያዘጋጃቸው ተውኔቶች በሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን የተደረሱ ሲሆኑ ታሪክ ጠቃሽና ረዣዥም ቃለ ተውኔት ናቸው።)

በወርልድ ኢንሳይክሎፒዲያ ኦፍ ኮንቴምፖራሪ ቴአትር እንደተገለጸው፣ አባተ ተውኔት ተመልካቹን በግሩም ሁኔታ መቆጣጠር የሚያስችል ክሂል ነበረው። በጸጋዬ የተተረጐሙት የዊልያም ሼክስፒር ማክቤዝ፣ ኦቴሎና ሐምሌት በታዳሚው ትውስታ ውስጥ የቃለ ተውኔቱ (ግጥም) ውበት ብቻ ሳይሆን፣ ተውኔታዊ ክዋኔዎች እንዲታወሱ የሆነው በአባተ መኩሪያ የአዘገጃጀት ስምረት ነው።

ራሱ ደርሶ ራሱ ያዘጋጀው «የሊስትሮ ኦፔራ» (1982) በወቅታዊ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ፤ በሙዚቃ የታጀበ ሥራው ለዓለም አቀፍ ሽልማት ያበቃው ጸሐፌ ተውኔት አባተ በኢትዮጵያ የተውኔት ታሪክ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፈው የቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤን «አፋጀሽኝ» ዳግም የመድረክ ብርሃን እንዲያይ ያደረገው እሱ መሆኑን ያስነበበን ደግሞ ጎልጉል ድረ ገፅ ነው።

በዩኔስኮ አፍሪካዊ ተውኔትን በደብሊን አቤይ ቴአትር እንዲያዘጋጅ የተመረጠው አባተ፣ የጸጋዬ ገብረ መድኅንን “Oda Oak Oracle” (የዋርካው ሥር ንግርት) ማዘጋጀቱን፤ ከእንግሊዛዊው ዕውቅ የቴአትር አዘጋጅ ሰር ፒተር ሆል ጋር በኮንቬንት ጋርደን ኦቴሎን ለማዘጋጀት ዕድል ማግኘቱን፤ መቀመጫውን በታንዛኒያ ያደረገውን የምሥራቅ አፍሪካ ቴአትር ኢንስቲትዩት በመሥራች አባልነትና በኃላፊነት ከመምራቱም ባሻገር፣ በአዲስ አበባ የመኩሪያ ቴአትር ስቱዲዮና መዝናኛ የተሰኘ ተቋምን መሥርቶ «ቴአትር ለልማት» የሚባለውን የተውኔት አቀራረብ ፈለግ መሠረት በማድረግ ብዙ ትምህርት ሰጪ ተውኔቶችን በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ተመሥርተው በማዘጋጀት ለመድረክ አብቅቷል።



ለመድረክ ካበቃቸው ተውኔቶች መካከል ሕሊና፣ ጠለፋ፣ ጀሮ ዳባ፣ በሐምሌ ጨረቃ ጉዞ፣ ድንቅ ሴት ሲጠቀሱ ከዘጋቢ ፊልሞችም የፍትሕ ፍለጋ እና የመስከረም ጥቃት የመሳሰሉት እንደሚገኙበት፤ መኩሪያ ስቱዲዮ በየክልሉና በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ አማተር ከያንያን የቴአትር፣ የሰርከስና የሙዚቃ ሥልጠና መስጠቱን፣ ከኢትዮጵያ ውጪም ወደ ተለያዩ አገሮች እየተጓዘ ትርኢት ማቅረቡን ... ድረ-ገፁ ይነግረናል።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን በእንግሊዘኛና በንኡስ ትምህርት (ማይነር) ድራማን በማጥናት ያገኘው ጋሽ አባተ (ሰኔ 1998 ዓ.ም ታትሞ የወጣው "መኩሪያ ቲአትር" መጽሔት የእንግሊዘኛ ቋንቋን በማጥናት ላይ እንዳሉ ዶ/ር ፊሊፕ በሚባለ የውጭ ዜጋ አማካኝነት "ኪነጥበብ ወ ቲያትር" የሚባል ክፍል ተቋቋመ እና የመጀመሪያው ተማሪ በመሆን ወደዚያ ተዛወሩ::” በማለት ማስፈሩ ይጠቀሳልና ወደ ፊት ይጠራል ብለን እንጠብቃለን)

አባተ መኩርያ በከተማ ጭብጦችና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተወስኖ የቀረ ምሁር አይደለም። እንደ ዘመነኞቹ (ተስፋዬ ገሠሠ፣ አፈወርቅ ተክሌ፣ ገብረክርስቶስ ደስታ፣ መንግሥቱ ለማ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ ፀጋዬ ገ/መድህን፣ ዳኛቸው ወርቁ እና ሌሎችም) ሁሉ ታሪካዊና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በግልፅ የሚያንፀባርቁ ስራዎችን ሰርቷል። ከእነዚህም አንዱ ”አድዋ” ሲሆን፤ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በዳግማዊ ምኒልክ ጠቅላይ አዝማችነት፣ በወራሪው የኢጣሊያ ሠራዊት ላይ ኢትዮጵያ የተቀዳጀችው ድል በየዓመቱ ሲዘከር በቴሌቪዥን መስኮት የሚታይ የቅድመ ጦርነት ዝግጅት የቪዲዮ ምሥል የአባተ መኩሪያ ትሩፋት ነው።

ለረጅም ዓመታት በአዲስ አበባ ትያትር እና ባህል አዳራሽ በስራ አስኪያጅነት ያገለገለው ጋሽ አባተ በ1950ዎቹ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «መዝናኛ በክዋኔ ጥበባት» (Entertainment in Performing Arts) በሚል ርዕስ በየሳምንቱ ዓርብ ለአንድ ዓመት የዘለቀ ፕሮግራም ማዘጋጀቱን (ፕሮግራሙም የአዝማሪ ጨዋታ በኢትዮጵያ ሕዝብና በክዋኔ ጥበባት ውስጥ የነበራቸውን ሚና ይዳስስበት፤ የተለያዩ ብሔረሰቦች ባህልን፣ እምነትን፣ ደስታን፣ ሐዘን፣ ወዘተ በጥበብ አንፃር ይታይበት፤ ቤተ ክህነት ለጥበቡ ዕድገት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ከታዋቂ የጥበብ ሰዎች ካበረከቱት ሥራ ጋር የሚቀርብበት እንደነበር ፕሮግራሙን በቅርበት የሚያውቁ ይናገራሉ።

”ጸጋዬ ገብረ መድኅን «የከርሞ ሰው» የሚለውን የጻፈውና ሙላቱ አስታጥቄ ለከርሞ ሰው ሙዚቃውን የሠራው በዚሁ የአባተ ፕሮግራም ነበር።” በማለትም በማስረጃ ያስረዳሉ።

አዲስ አበባ ከተማ የተመሠረተችበት 100ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በዓል ሲከበር ለበዓሉ ድምቀት ከተዘጋጁት አንዱ ንጉሠ ነገሥቱ «ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት» ብለው ለዘመቻ ሲነቃነቁ ባለፉበት በባልደራስ አካባቢ በሚገኘው የቀበና ወንዝ ነባር ድልድይ አጠገብ አዲስ የተሠራው «የዓድዋ ዘመቻ መታሰቢያ ድልድይ» የተመረቀው የዚያን ዘመን የክተት ስሪት በሚያሳይ መልኩ አምሳያ የተፈጠረላቸው ንጉሠ ነገሥቱን፣ እቴጌይቱን፣ መኳንንቱን፣ የጦር አዝማቾችን፣ ዘማቾቹን፣ ሴቶች አገልግል ተሸክመው ሁሉም እየፎከሩ እየሸለሉ የሚያሳየውን «የራስ አባተ ጦር እለፍ ተብለሃል...» ወዘተ እየተባለ በ400 ተሳታፊዎች የቀረበው ክዋኔ ለዘመን ተሻጋሪነት የበቃው በመራሄ ተውኔት አባተ መኩሪያ መሆኑን ከላይ የጠቀስነው ምንጫችን ያስያል። አባተ ዓድዋንና ድሉን የሚዘክር ላቅ ያለ ይዘት ያለውን የዓድዋ ፊልም ፕሮጀክትን ቢቀርጽም (ለህዝብም በይፋ ተገልፆ ነበር)፣ በወቅቱም በ35 ሚሊዮን ብር በጀት ሊሠራ መታቀዱንና ፕሮጀክቱን ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ በበላይ ጠባቂነት እንደያዙት ቢነገርም እስካሁን ድምፁ እንዳልተሰማ ለንባብ አብቅቷል።

በ1988 “ኤዲፐስ ንጉስ”ን የመደረከው፤ በተወለደ በ76 ዓመቱ ሐምሌ 14 ቀን 2008 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለየን ጋሽ አባተ ሙያውን ከማበልፀግ አኳያም በርካታ ስራዎችን የሰራ ሲሆን፤ በተለይም ኃላፊነትን በአግባቡ ከመወጣት አኳያ የሄደበት ርቀት ቀላል አይደለም።

በወቅቱ ከተነገረውም ሆነ በተለያዩ ሚዲያዎች ሲንሸራሸሩ ከነበሩት መረጃዎች፤ እንዲሁም ከጋሽ አባተ የህይወት ታሪክ መረዳት እንደ ተቻለው፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት (የአሁኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር) የቴአትር ዳይሬክተር፣ እንዲሁም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኪነ ጥበባት ወቴአትር (ባህል ማዕከል) ዳይሬክተር ሆኖ ሠርቷል።

አባተ ከብሔራዊ ቴአትር ሌላ በአገር ፍቅር ቴአትር፣ በአዲስ አበባ ባህልና ቴአትር አዳራሽ በአዘጋጅነት፣ በጸሐፌ ተውኔትና መራሔ ተውኔትነት፤ እንዲሁም በኃላፊነት ጭምር አገልግሏል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግሏል።

የጋሽ አባተ መኩሪያ የስራ ባልደረባ የቅርብ ወዳጁ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጥበባት ኮሌጅ ዲን የነበረው አቶ ነቢዩ ባዬ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባህል ማዕከል «ዝክረ አባተ መኩሪያ» ብሎ ባዘጋጀው መድረክ ላይ ስለ ጋሽ አባተ «አባተ የዩኒቨርሲቲ የቴአትር ትምህርት በትክክለኛው መሠረት ላይ እንዲገኝ የላቀ ሚና ተጫውቷል። በዩኒቨርሲቲው የኪነ ጥበብ የፈጠራ ማዕከል እንዲቋቋም አሻራውን አኑሯል። የተለያዩ የቴአትር ንድፈ ሐሳቦችን በማቅረብ ግንባር ቀደም አርቲስት ነው።» በማለት የሰጠው ምስክርነት ጋሽ አባተን በሚገባ ይገልፀዋልና እዚህም ደግመን ልንጠቅሰው ግድ ብሎናል። ለሌላ ተጨማሪ ሀሳብም የፋንታሁን እንግዳን «ታሪካዊ መዝገበ ሰብ» መመልከት ተገቢ ይሆናል።

ጋሽ አባተ ለሙያዊ አስተዋፅኦና የተዋጣለት መምህርነቱ ብዙዎች የሚመሰክሩለት ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል ፍቃዱ ተክለ ማሪያም እና አበበ ባልቻ ይገኙበታል።

ፍቃዱ በህይወት በነበረበት ወቅት ስለ ጋሽ አባተ ተጠይቆ ሲመልስ «ራሴን ፈልጌ እንዳገኝ የገራኝ፣ መንገዱን ያሳየኝ፣ የገሰፀኝ፣ ዛሬ ለደረስኩበት ደረጃ ያበቃኝና ያሳደገኝ የጥበብ አባቴ ነው» ማለቱና አርቲስት አበበ ባልቻም በተጠየቀ ቁጥር ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተያየቱን ሲሰጥ መስማት ስለ ጋሽ አባተ ሙያዊ አስተዋፅኦ ለመረዳት በቂ ነው ማለት ይቻላል።

አባተ መኩሪያ ሙያተኛ ብቻ ሳይሆን ለሙያው ማደግም ሁሌ እንደሚጨነቅ የሚያውቁት ብቻም ሳይሆኑ፤ ስለ’ሱ የከተቡ ሁሉ ይመሰክሩለታል። ለዚህም «ታሪካዊ መዝገበ ሰብ» ላይ «የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ባህል አትኩሮ የሚያጣጥምና የሚወድ ነው። ቴአትር ቤቱ ይሞላል። ግን ከቴአትር አንፃር (ከድርሰቱ) ያየነው እንደሆነ ብዙ የሚተቹ ነገሮች አሉ። እንደ ቴአትር አዋቂ ተመልካች ቴአትሮቹን ብናያቸው ብዙ ግድፈቶች እናገኛለን። ተመልካቹ ለዚያ ሁሉ ደንታ የለውም። የራሱን ሕይወት ማየት ይወዳልና ይመጣል። በአሁኑ ጊዜ ጥበቡ ሳይሆን ተመልካቹ ነው የሚፈታተነን። ደግሞ የኛን አገር ቴአትር እንዳያድግ የገደለው ቴአትር ቤቶች በመንግሥት እጅ መሆናቸው ነው። ቴአትር ቤቶች አንድ ዓይነት ሥራ ነው የሚሠሩት።» በሚል የሰፈረውን መጥቀስ ይበቃል።

ሰኞ ኅዳር 10 ቀን 1932 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አዋሬ ሠፈር ከአባቱ ከአቶ ስለሺ ማንደፍሮና ከእናቱ ከወ/ሮ ውብነሽ መኩሪያ የተወለደው አባተ መኩሪያ በዚህ ሁሉ የሙያና አገልግሎት ዘመኑ ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ እንዳልሆነለት ይነገራል። በርካታ መሰናክሎች አጋጥመውት የነበረ መሆኑም እንደዛው።

ምንጮቻችን ላይ ሰፍሮ እንዳገኘነው ቀዳሚው ፈተና በአአ ዩኒቨርሲቲ፣ ከትምህርቱ ጐን ለጐን በኪነ ጥበብ ወቴአትር (ክሬቲቭ አርት ሴንተር) በሚሠራበት ወቅት በነበረው የግጥም ጉባኤ ባለቅኔው ዮሐንስ አድማሱ ያቀረበው፤


**ሳም እሳት ወለደች በሬ ቀንድ አወጣ፣**
**በሥልጣን ሲቅ መሆን ይህም አለ ለካ።**

ግጥም በዩኒቨርሲቲው ኃይለኛ ቁጣ በመቀስቀሱ (ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያምን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አድርገው መሾማቸውን የሚኃንጥ በመሆኑ) ማዕከሉ ይዘጋል። አባተን ጨምሮ ሁሉም ባልደረቦቹ እንዲባረሩ መደረጉ አንዱ ነው። (ዮሐንስ አድማሱ ይህን ቅሬታ የሚያባብስ ግጥም በመግጠማቸው "ኪነጥበብ ወቲያትር" በሣምንቱ በእሣቸው ትዕዛዝ እንዲዘጋ፤ የክፍሉ ኃላፊ ዶ/ር ፊሊፕ ካፕላንም ኮንትራታቸው እንዲቋረጥ መደረጉን፤ እሱና ጓደኞቹ ከ"ኪነ ጥበብ ወቲያትር” መባረራቸውን ... በህይወት እያለ ለመኩሪያ ቲአትር መጽሔት በሰጠው ቃለ መጠይቅ ተናግሯል።)

አቶ አባተ ከዩንቨርሲቲው "ኪነጥበብ ወቲያትር” ከተባረረ በኋላ አዲስ በመቋቋም ላይ በነበረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በአዘጋጅነት ተቀጠረ:: ቴሌቪዥን ሥራውን በጀመረ ጊዜ የሚያስተዳድሩት እንግሊዞች ስለነበሩ አቶ አባተ ለአራት ወራት እንዳገለገለ ግላስኮት ቴሌቪዥን ኮሌጅ ውስጥ ገብቶ እንዲማር ወደ እንግሊዝ አገር ተላከ:: በእንግሊዝ አገር ቆይታው ሚዲያ ኮሚዩኒኬሽን አጥንቶ፤ በቢቢሲ ጣቢያም በመስራት የሥራ ልምድ አግኝቶ ወደ አገሩ ተመለሰ:: ከዚያ እንደተመለሰ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና በአገር ፍቅር ቲያትር ቤት አዘጋጅ፤ እንዲሁም አሰልጣኝ በመሆን ቀጠለ:: በመሃሉ የሲኒማቶግራፊ ትምህርት የመማር እድልን አግኝቶ ወደ ጀርመን መሄዱም የታሪኩ አካል ሆኖ ይነገርለታል።

የሁለት ልጆች አባቱና አንጋፋው አርቲስ አባተ መኩሪያ በሰባ ስድስት ዓመቱ ከዚህ አለም ሲለይ ”ተንቀሳቃሹ ቴአትር ቤት አረፈ” ነበር የተባለለት። ወደ ፊት ህይወትና ስራዎቹን በተመለከተ በሚገባ እንደሚጠና፤ በርካታ መረጃዎችንም እንደምናገኝ በመተማመን ለዛሬ በዚሁ እናብቃ።

# ስፖርት





## የንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን ዛሬ በሴካፋ የግማሽ ፍጻሜ ወሳኝ ፍልሚያ ይጠብቀዋል

ብርሃን ፈይሳ



**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ክለብ የዛሬውን ጨዋታ በመርታት ለፍጻሜው እንደሚያልፍ ይጠበቃል፤**

ካለፈው ዓመት አንስቶ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) መካሄድ ከጀመሩ ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ (ሴካፋ) የክለቦች ቻምፒዮና ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ በታንዛኒያ እየተካሄደ ይገኛል። አንድ ሳምንት ያስቆጠረው ይህ ውድድር የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታዎችን ዛሬ ይስተናግዳል። ከምድቡ አንደኛ ሆኖ ያለፈው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብም ከዩጋንዳው ሺ ኮርፖሬት ጋር ለፍጻሜ ለማለፍ ይፋለማል፡፡ ሌላኛው የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታ ደግሞ በታንዛኒያው ሲምባ ኩዊንስ እና በሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ ጋር ይደረጋል፡፡

በታንዛኒያ አሩሻ አስተናጋጅነት ለሁለተኛ ጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው የሴካፋ ክለቦች ቻምፒዮና ከቀጠናው የተወጣጡ ስምንት ክለቦችን በሁለት ምድብ ከፍሎ ሲያፋልም ቆይቷል፡፡ ወደ አፍሪካ ቻምፒዮንስ ሊግ የሚያልፈውን አንድ ቡድን ለመለየት በሚያስችለው በዚህ ቻምፒዮና ዛሬ የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታዎች የሚደረጉ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ሶስቱንም የምድብ ጨዋታዎች በማሸነፍ የምድቡ ቀዳሚ ክለብ ሆኖ የጨረሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቡድን ለፍጻሜ የሚያበቃውን ወሳኝ ጨዋታ ያደርጋል፡፡ ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ጊዜ በመድረኩ የወከለውና የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪምየር ሊግ ቻምፒዮኑ ንግድ ባንክ በምድብ ሁለት የተደለደለውን የዩጋንዳውን ሺ ኮርፖሬት ያስተናግዳል፡፡

እንዳለፈው ዓመት ሁሉ በዚህ ቻምፒዮና ላይም ድንቅ ብቃቱን እያስመሰከረ የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመጀመሪያ ጨዋታውን ከዛንዚባሩ ዋሪየር ኩዊንስ ጋር በማድረግ 9 ለ 0 በሆነ ሰፊ ወጤት መርታቱ የሚታወስ ነው፡፡ በአዛም ኮምፕሌክስ ስታዲየም በተካሄደው ሁለተኛው የምድብ ማጣሪያ ጨዋታው ደግሞ የቡሩንዲውን ፎፊላ ፒኤፍ 5 ለ 1 በማሸነፍ አንድ ቀሪ ጨዋታ እያለው ከምድቡ ማለፉን አረጋግጧል። በጨዋታውም አምበሏ ሎዛ አበራ 3፣ መዲና ዓወልና ናርዶስ ጌትነት ደግሞ አንድ አንድ ግቦችን ማስቆጠር ችለዋል፡፡ በቤንጃሚን ማካፓ ስታዲየም ከሩዋንዳው ክለብ ኤ ኤስ ኪጋሊ ጋር በነበረው የምድቡ የመጨረሻ ጨዋታም ንግድ ባንክ 2 ለምንም በማሸነፍ ምድቡን በአንደኝነት አጠናቆ ግማሽ ፍጻሜውን ተቀላቅሏል። በዚህም የቻምፒዮናው ከፍተኛ ግብ አስቆጣሪዋ ሎዛ አበራ 9 ግቦችን ከመረብ በማሳረፍ መሪነቷን አጠናክራ ቀጥላለች፡፡ መዲና ዓወል ደግሞ በ6 ግቦች ትከተላታለች፡፡

በቻምፒዮናው መርሃ ግብር መሰረትም የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታዎቹ በታንዛኒያ ብሄራዊ ስታዲየም በአንድ ሰዓት ልዩነት ይደረጋሉ፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ከዩጋንዳው ሺ ኮርፖሬት እንዲሁም በታንዛኒያው ሲምባ ኩዊንስ እና በሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ መካከል ይደረጋሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ዋና አሰልጣኝ ብርሀኑ ግዛው፤ ቡድኑ ሶስቱንም ጨዋታዎች በማሸነፉ የተሰማውን ከፍተኛ ደስታ ገልጸዋል። አሰልጣኝ ብርሃኑ አክሎም «የቡድናችን የመጀመሪያው ግብ ግማሽ ፍጻሜውን መቀላቀል ነበር፤ አሁን ደግሞ የመጨረሻውን ነጥብ ለማምጣት ዝግጁ ነን» ማለቱን ካፍ በድረ ገጹ አስነብቧል፡፡

የንግድ ባንክ ተጋጣሚ የሆነው ሺ ኮርፖሬት በምድብ ሁለት 6 ነጥብ በመሰብሰብ ሁለተኛ በመሆን ወደ ግማሽ ፍጻሜው ያለፈ ሲሆን፤ በሲምባ ኩዊንስ ከደረሰበት የ2ለባዶ ሽንፈት ውጪ ሁለቱን ጨዋታዎች ማሸነፍ የቻለ ክለብ ነው፡፡ ይህም አንድም ሽንፈት ያላስተናገደውና በአምናው ቻምፒዮና ሁለተኛ በመሆን ያጠናቀቀው ንግድ ባንክ ፈተና ሊሆን እንደሚችል ነው የሚጠበቀው። በምድብ አንድ ሁለተኛ ቡድን በመሆን ለዛሬው ግማሽ ፍጻሜ የደረሰው ኤኤስ ኪጋሊም ከምድብ ሁለት ቀዳሚ በሆነውና ጠንካራው ክለብ ሲምባ ኩዊንስ መፈተኑ አይቀሬ ነው፡፡

በውድድሩ ላይ ስምንት ቡድኖች ተካፋይ ሲሆኑ፤ በሁለት ምድብ ተከፍለውም የዋንጫ ፍልሚያቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በመጀመሪያው ምድብ የተደለደሉት የኢትዮጵያውን ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ጨምሮ፤ የዛንዚባሩ ዋሪየርስ ኩዊንስ፣ የብሩንዲው ፎፊላ ፒኤፍ እና የሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ ናቸው፡፡ በሌላኛው ምድብ ደግሞ የአዘጋጇ ሃገር ታንዛኒያ ክለብ የሆነው ሲምባ ኩዊንስ፣ የጅቡቲው ጋርዴ ሪፐብሊካን፣ የዩጋንዳው ሲ ኮርፖሬት እንዲሁም የደቡብ አፍሪካው ዩ ጆይንት ስታርስ ነበሩ፡፡ የፍጻሜ እና የደረጃ ጨዋታዎቹም በመጪው ቅዳሜ ነሃሴ 21/2014 ዓም እንደሚካሄዱ ታውቋል፡፡


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

## መለያ ቁጥር ኢ/ስ/አ/04-2015

የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ለ2015 በጀት ዓመት ሊያስጠግነው ያሰበውን ትልቁን የእግር ኳስ ሜዳ እና የአሸዋ የልምምድ መሮጫ ጥገና ሥራ ግዢዎችን ከዚህ በታች በተገለጸው መስፈርት መሰረት አወዳድሮ በአገር አቀፍ ግልፅ ጨረታ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶችን በጨረታው እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. ተጫራቾች በገፀ ምድር ማስዋብ እና ተያያዥ ሥራዎች ዘርፍ ፍቃድ ያለውና ለ2014 ዓ.ም የታደሰ፤
2. ከላይ የተጠቀሰውን ሥራ አግባብነት ያለው ንግድ ፍቃድ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ ታክስ ክሊራንስ የሚያቀርቡ፣ የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፣ በአቅራቢነት የተመዘገቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ የብር መጠን 150,000.00 (መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፤
4. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 400 (አራት መቶ ብር) በመክፍል ጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዶቻቸውን በታሸገ ኢንቨሎፕ ይህ ማስተወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 የስራ ቀናት በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በ4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ 16ኛው ቀን በዓል ወይም የዕረፍት ቀን ከሆነ በቀጣይ ባለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የቴክኒካል ኦሪጂናልና ኮፒ ሰነዶችን እንዲሁም የፋይናንሻል ኦሪጂናልና ኮፒ ሰነዶችን ለየብቻው በአራት ፖስታ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም ሲፒኦ በቴክኒካል ኦሪጂናል ሰነድ(ፖስታ) ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. አካዳሚው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. አድራሻ፡- የቀድሞ ኢምፔሪያል አደባባይ አካባቢ ግዢና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 112
10. ስልክ ቁጥር 0116673664

**የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ**



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

## ለአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባላት በሙሉ

አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት መስከረም 12 ቀን 2015 ዓ.ም በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል (በቀድሞው ኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል) ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ያካሂዳል። የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንትና የቦርድ አባላት ምርጫም ይካሄዳል።

ይህ ምርጫ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከፍተኛ ልምድና የሥራ ፍላጐት ያላቸው አባላት የሚገኙበት የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቋቁሟል። ኮሚቴው ለፕሬዚዳንትነት፣ ለም/ፕሬዚዳንትነትና ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ቦታዎች የሚጠቆሙትን ዕጩዎች ይቀበላል።

ስለሆነም የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባላት ለዕጩዎች በወጣው መስፈርት መሠረት ለተጠቀሱት ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ራሳችሁንም ሆነ ብቃት ያላቸውን ሌሎች አባላት እንድትጠቁሙ ጥሪ እናቀርባለን።

ለጥቆማውም ከምክር ቤቱ ዋና ፅሐፊ ቢሮ ወይንም ከምክር ቤቱ ድረገጽ ላይ (www.addischamber.com) የመስፈርቱን ዝርዝር እና የዕጩዎች መጠቆሚያ ቅጽ በመውሰድ ከሞላችሁ በኋላ የተሞላውን ቅጽ በኤንቨሎፕ አሽጋችሁ አድራሻውን "**ለምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ**" በሚል አስፍራችሁ እስከ ነሀሴ 30 ቀን 2014 ዓ/ም ከቀኑ 11 ሰዓት ድረስ ለአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፅሐፊ ቢሮ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀው የጥቆማ ሳጥን ውስጥ እንድታስገቡ ከአደራ ጭምር እናሳስባለን።

**ለተጨማሪ መረጃ፣**

በስልክ ቁጥር 011 5513814፣ 5519817፣5514517፣5528205፣ 5518055 የውስጥ መስመር 214/222/202

በመደወል የምክር ቤቱን ባልደረቦች ማነጋገር ይቻላል።

**አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት**